«ጾም ልጓም ፍሬሐ ጥዑም ትሕተ ኢናምስላ ለጾም ፤
ጾም ልጓም ናት ፍሬዋም ጣፋጭ ነው ጾምን
የተናቀች አናድርጋት»

*ቅዱስ ያሬድ (ጾመ ድጓ)*

# ስምዐ ጽድቅ



## ማውጫ


፪ አጫጭር ዜናዎች

፬ መልእክት

፮ ሪፖርታዥ

፱ ቤተ አብርሃም

፲፫ ቃለ መጠይቅ

፲፮ የሕፃናት ዓምድ

፲፰ ትዝብት

፳ ምሥጢሬን ላካፍላችሁ



## ስምዐ ጽድቅ

የቤተ ክርስቲያኒቱን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓትና ትውፊት ጠብቆ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ማኅበረ ቅዱሳን በትምህርትና ሐዋርያዊ አገልግሎት ማስተባበሪያ በጋዜጣ ዝግጅት ክፍል እየተዘጋጀ በወር ሁለት ጊዜ የሚወጣ መንፈሳዊ ጋዜጣ

ጳጉሜን ፫ ቀን ፲፱፻፹፫ ዓ.ም. ተጀመረ



☎ 011-1553555/ 011-1553442

✉ 80078

አዲስ አበባ

ምክትል ዋና አዘጋጅ
ወርቅነሽ ቱፋ

ከፍተኛ ሪፖርተር
ካሣሁን ለምለሙ

ሪፖርተር
ረቂቅ መቻል

የገጽ መልክ (Layout) ዲዛይነር
ግደይ ገብሬ

ጸሐፊ
ገነት ታደሰ

የዝግጅት ክፍሉ ኢሜይል
newspaper@eotcmk.org

# መንግሥት ለአብያተ ክርስቲያናት፣ ለቅርሶችና ምእመናን የሕግ ከለላ እንዲሠጥ ተጠየቀ

*በካሣሁን ለምለሙ*

መንግሥት ለአብያተ ክርስቲያናት፣ ለቅርሶችና ምእመናን የሕግ ከለላ እንዲሠጥ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለሃይማኖት ጠየቁ::



*ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት*

ቅዱስነታቸው ይህንን የጠየቁት የዐቢይ ጾም መግባቱን አስመልክቶ የካቲት ፳፱ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም በጽሕፈት ቤታቸው ለጋዜጠኞች ጋዜጣዊ መግለጫ በሰጡበት ወቅት ነው::

በአንዳንድ የሀገራችን ክፍሎች በተከሠተው ችግር ምክንያት ብዙ ኢትዮጵያውያን ለርኀብ፣ ለእርዛትና መፈናቀል መዳረጋቸውን ያነሡት ቅዱስነታቸው ችግሩ ኢትዮጵያውያንን ብቻ ሳይሆን መላው ዓለምን ያሳሰበ ጉዳይ እንደሆነ ተናግረዋል::

ይህም ሆነው በሀገራችን በተከሠቱ ችግሮች ምክንያት በውስጣችን ፍቅርና ሰላም በመጥፋቱ ነው ያሉት ቅዱስነታቸው ችግሮቹ መፍትሔ እንዲያገኙ ሁሉም ወገን ያላሠለሰ ጥረት እንዲያደርግ መክረዋል:: አብዝተን ልንሠራው ከሚገባው ነገር

ሁሉ ሰላም፣ ፍቅር፣ ስምምነት፣ ይቅርባነት፣ መተጋገዝ፣ መራራትና ካለው ላይ አካፍሎ ለሌላው መሥጠት ሊሆን እንደሚገባም ቅዱስነታቸው አስረድተዋል::

ከዚህ በኋላ በሀገራችን የሰው ሕይወት እንዳይጠፋ፣ አብያተ ክርስቲያናት እንዳይደፈሩ፣ ንዋየ ቅድሳትና

ቅርሶች እንዳይዘረፉ መንግሥት ድርጊቱን በማስቆም ለሁሉም የሕግ ከልላ እንዲያደርግላቸው ቅዱስነታቸው አሳስበው የሃይማኖት ተቋማት፣ ማኅበረሰቡና በጎ አድራጊዎችም በችግር ላይ ያሉ ወገኖችን በመደግፍ የበኩላቸውን እንዲወጡ ጥሪ አቅርበዋል::



# ትውልዱ የቅዱስ ያሬድን ትሩፋቶች በተገቢ መንገድ እንዳልተጠቀመባቸው ተገለጠ

*በካሣሁን ለምለሙ*

ትውልዱ፣ቤተ ክርስቲያንና ሀገር የቅዱስ ያሬድን ትሩፋቶች በተገቢ መንገድ እንዳልተጠቀሙባቸው የደብረ ሐዊ ቅዱስ ያሬድ አንድነት ገዳም ፕሮጀክት አቢይ ኮሚቴ ም/ሰብሳቢ የነበሩት ላእከ ሰላም ባያብል ሙላቴ ገለጡ::

ላእከ ሰላም ባያብል ሙላቴ ይህንን የገለጡት በሰሜን ጎንደር ሀገረ ስብከት በበየዳ ወረዳ ጥጉና ጣና ቀበሌ የሚገኘው የደብረ ሐዊ ቅዱስ ያሬድ አንድነት ገዳም ፕሮጀክትና ዘጋቢ ፊልም የካቲት ፬ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም በኢንተር ኮንትኔታል ሆቴል ይፋ በሆነበት ወቅት ተገኝተው ባስተላለፉት መልእክት ነው::

ወደ ገጽ ፫ ዞሯል

## ትውልዱ የቅዱስ ያሬድን ትሩፋቶች ...

በደብረ ሐዊ ቅዱስ ያሬድ አንድነት ገዳም እንዲሠራ የታሰበው ፕሮጀክት ትውልዱ የቅዱስ ያሬድን አሻራዎች እንዲረዳና ከትሩፋቶቹም ተጠቃሚ እንዲሆን ያደርጋል ያሉት ላእከ ሰላም ባያብል ገዳሙ ያልተበረዘ ሁሉን ዓይነት የአብነት ትምህርት የሚሰጥ ማእከል በመሆኑ የዕውቀትና ኪነ ጥበብ ምንጭ ይሆናል ሲሉ ተናግረዋል።

ቅዱስ ያሬድ ለኢትዮጵውያንና ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዘመን የማይሽረው አስተዋጽኦ ያበረከተ ሊቅ መሆኑን ላእከ ሰላም ባያብል ከጠቆሙ በኋላ "በገዳሙ ተግባራዊ የሚሆነው ፕሮጀክት ሲጠናቀቅ ለቤተ ክርስቲያንና ለሀገር የተለየ ድርሻ ይኖርዋል" ብለዋል።

ገዳሙ ከሰሜን ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ አዋሳኝ በመሆኑ በተለይ የውጭ ሀገር ቱሪስቶች መጥተው በሚጎበኙበት ወቅት ሀገርና ገዳሙ ከውጭ ምንዛሬ ተጠቃሚ እንደሚሆን ላእከ ሰላም ባያብል ተናግረዋል። ገዳሙ ፲፱፻፷፪ ዓመታት ታሪክ ባለቤት በመሆኑም ከሌሎች አካባቢዎች በተለየ ሁኔታ ሊጎበኝ እንደሚችልም አስረድተዋል።

የሰሜን ወሎና ከሚሴ አህጉረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ኤርምያስ በመርሐ ግብሩ ላይ ተገኝተው ባስተላለፉት መልእክት ጥዑመ ልሳን ቅዱስ ያሬድ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መልክና ውበት እንደሆነ ገልጠው "የእርሱን ሁለንተናዊ ሀብት ሊያሳይ የሚችል ፕሮጀክት እስከ አሁን ድረስ ያለመሠራቱ የሀገርና የቤተ ክርስቲያን ጉድለት ነው" ብለዋል።

ብፁዕነታቸው አያይዘው ‹‹በዚህ ወቅት ቅዱስ ያሬድን የሚዘክሩ ዘጋቢ ፊልሞችና ፕሮጀክቶች መዘጋጀታቸው መልካም ጅምር ነው። ፕሮጀክቶቹ የዘገዩ ቢሆንም ከአሁን በኋላ ለሚመጣው ትውልድ አቅምና ጉልበት ይሆናሉ›› ሲሉ ተናግረዋል። ቅዱስ ያሬድ የዜማ ሊቅ ብቻ እንዳልሆነ፤ ብሉያትንና ሐዲሳትን፣ ሊቃውንትን እንዲሁም አዋልድ መጻሕፍትን ጭምር የተረጎመ፤ ያብራራና ያመሰጠረ መሆኑንም አስረድተዋል።

የጥበብ ምንጭ የሆኑትን የጥዑመ ልሳን ቅዱስ ያሬድን ትሩፋቶች ደራሲያንና የዜማ ሰዎች በደንብ ሊጠቀሙባቸው እንደሚገባ ያሳሰቡ ሲሆን በደብረ ሐዊ ቅዱስ ያሬድ አንድነት ገዳም ሊተገበር የታቀደውን ፕሮጀክት እውን ለማድረግ በየትኛውም ዓለም ያለ ሕዝበ ክርስቲያን የድርሻውን ሊወጣ ይገባል ሲሉ ጥሪ አቅርበዋል። የቤተ ክርስቲያን ሀብቶች የሀገር ሀብቶች መሆናቸውን በመረዳት መንግሥትም ቤተ ክርስቲያን የምታከናውነውን የልማት ሥራ ሊያግዝ ፤እንዲሁም የሚያሥፈልጉ መሠረተ ልማቶችን ሊያሟላ እንደሚገባም ተናግረዋል።

የጠቅላይ ሚንስትሩ የማኅበራዊ ጉዳዮች አማካሪ ሙሓዘ ጥበባት ዲ/ን ዳንኤል ክብረት በበኩላቸው ቅዱስ ያሬድን የሚዘክሩ ሥራዎች እንዳልተሠሩ አስታውቀው ያሁኑ ትውልድ እርሱን የሚዘክሩ ሥራዎች በመሥራት ቀሪውን ደግሞ ለመጭው ትውልድ የቤት ሥራ ትቶ ማለፍ እንደሚያስፈልግ አንስተዋል።

የደብረ ሐዊ ቅዱስ ያሬድ አንድነት ገዳም ፕሮጀክት የወቅቱ ዐቢይ ኮሚቴ ም/ሰብሳቢ አቶ ታደሰ አለማየሁ በዕለቱ ባቀረቡት ሪፖርት እንዳስታወቁት ጥዑመ ልሳን ቅዱስ ያሬድን በመላው ዓለም ለማስተዋወቅ የተደገው ጥረት አናሳ መሆኑን አስረድተው በሀገር አቀፍ ደረጃ ለማስተዋወቅ የሚያግዝ ፕሮጀክት ተቀርጾ ወደ ተግባር ሊገባ እንደሆነ አስረድተዋል።

በሰሜን ጎንደር ሀገረ ስብከት በበየዳ ወረዳ በጥጉና ጣና ቀበሌ የሚገኘው የቅዱስ ያሬድ አንድነት ገዳም ፪ ሺህ ተማሪዎችን የሚያስተናግድ የአብነት ትምህርት ቤትን ጨምሮ ሌሎች ፕሮጀክቶች ተግባራዊ እንደሚሆኑ ያስገነዘቡት ም/ሰብሳቢው ገዳሙን የልሕቀት ማዕከል ለማድረግ እየተሠራ እንደሆነም ተናግረዋል።

ከአብነት ትምህርት ቤቱ በተጨማሪ በገዳሙ ግዙፍ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያንን ጨምሮ የቅዱስ ያሬድን ሥራዎችና ተጋድሎዎች የሚያሳይ ዘመናዊ ሙዚየም እንደሚሠራ ያስረዱት ሰብሳቢው ገዳሙ ከተለያየ ዓለም ለሚመጡ ጎብኝዎች መዳረሻ ለማድረግ በትኩረት እየተሠራ እንደሆነና የፕሮጀክቱ ሥራዎች በቅርቡ ለመጀመርም በሀገር አቀፍ ደረጃ ኮሚቴ ተዋቅሮ እንቅስቃሴ መጀመሩን አስታውቀዋል።

# የተቸገሩትን ለመርዳት የእግዚአብሔር እጆች እንሁን!

ሀገራችን ኢትዮጵያ ከምን ጊዜውም በላይ በችግር ላይ የወደቀችበት ሰዓት ነው፡፡ ከከተማ ወጣ ብለው በሚገኙ አካባቢዎች እና በተለያዩ ክልሎች የሚኖሩ ዜጎች ወቅትን ተከትሎ በመጣው ግርግር ውስጥ የጥቃት ሰለባ ሆነዋል፤ ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለዋል፤ በእሳት ተቃጥለዋል፣ በሰይፍ ተገድለዋል፤ በአንድ ጀንበር ከባለንብረትና ከባለሀብትነት ማማ ላይ ወርደው የሰውን እጅ የሚጠብቁ ተረጂዎች ሆነዋል፡፡

የመንግሥት ለውጥን ተከትሎ የመጣው ይህ ‹‹ሌሎችን›› የማጥቃት ሂደት ይበርዳል ሲባል እየጋለ፤ ይቀንሳል ሲባል እየጨመረ፣ መልኩን እየቀያየረ እዚህ ደርሷል፡፡ ዛሬም ንጹሐን ዜጎች ይገደላሉ፣ ይዘረፋሉ፣ እንዲሰደዱ ይደረጋሉ፡፡ አንድ ቦታ ቀዝቀዝ ሲል ሊላው ጋር እየሞቀ መላ ሀገሪቷን ያዳረሰው ይህ ክፉ ወረርሽኝ የእያንዳንዱን ቤት እያንኳኳ ‹‹ የነገ ተረኛ ማነው?›› የሚያስብል ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡

እንደ አየሩ ፀባይ የሚለዋወጠው ይህ የጥቃት ዒላማ ሲያሻው ፖለቲካዊ እየሆነ ፤ሲያሻው ብሔር ላይ እያተኮረ፤ አሊያም ጉዳዩን ሃይማኖታዊ አድርጎ ‹‹ከእኔ ውጪ ነው›› ከሚለው ሃይማኖት ተከታይ ላይ የጥፋት ቃታውን እየሳበ እዚህ ደርሷል፡፡ ከኢትዮጵያዊ ባህልና ወግ በተፋታ መልኩ የሞቱ በወግ ባልተቀበሩበት ቀዬ በሕይወት የተረፉቱ ለረኀብና ለእርዛት እንዲሁም ለመጠለያ እጦት ተዳርገው ይገኛሉ፡፡

ጉዳዩን በአንድ ሰሞን ሞቅታ ውስጥ ብቻ አይተን ሰሞነኛ ሐዘን እና ርዳታ ብቻ በማድረግ ሥራ ተጠምደን ስናበቃ በወረት የምንተወው የንፁሀን ሕይወት የሚገደን መቼ ነው? ለችግረኛ የሚዘረጋው ኢትዮጵያዊ እጅ ወዴት አለ? ያስብላል፡፡ ግማሽ አካላችን ለከፋ አደጋ ተጋልጦ ባለበት በዚህ ወቅት የእግዚአብሔር ልጆች ክርስቲያኖች ወዴት ናቸው? በየጊዜው እየጨመረ የመጣው ኦርቶዶክስ ተኮር የሆነው ጥፋት ከምእመን ወደ ቤተ ክርስቲያን እየተዛመተ የ፫ ሺህ ዘመን ታሪክ ያላትን ሀገር እንደ ሰደድ እሳት እየበላ ሲጨርስ ዝም ማለት ከታሪክ ተወቃሽነት አያድንም፡፡ ሀገርን እንደባላ አቁማ የያዘች ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ታሪክ አልባ ፣ ቅርስ አልባ እየሆነች ባለችበት በዚህ ሰዓት ምእመናንዋንም ሆነ አብያተ ክርስቲያን የሚጠብቅ፣ የሚንከባከብ እንዲሁም በፈረሰው በኩል የሚቆም ምእመን ዛሬ ያስፈልጋታል፡፡

ከሀገሪቱ ሕዝብ ከሃምሳ ፐርሰንት በላይ ምእመን ያላት፤ የሀገሪቱ ዋንኛ የቱሪስት መዳረሻ የሆኑ ቅዱሳት መካናት ባለቤት የሆነች ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሰው አልባ ፣ ምእመን አልባ አብያተ ክርስቲያናት እና ገዳማት አልባ እየሆነች እያደር እያነሰች እና ቀድሞ ከነበረችበት የልዕልና ማማ ላይ በፍጥነት እየወረደች መሆኑን በውል ተገንዝቦ ከሰሞነኛ ግርግርታ ወጥቶ በጽሞና ማሰብ ይጠይቃል፡፡ እንደ አንድ የቤተ ክርስቲያን ልጅ እየጠፉ ያሉትን የቤተ ቅዱሳት መካናት ላይ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት ፣ የተጎዱ ወገኖችን በማሰብ ፤ለርዳታ እጅን መዘርጋት እና ዘላቂ መፍትሔን በማፈላለግ የድርሻን መወጣት ወቅቱም ክርስትናችንም የሚጠይቀው ነው፡፡

በአርአያ ሥላሴ የተፈጠሩ ሰዎች በእርስ በርስ ግጭት፣ ዘርና ሃይማኖት ተኮር በሆነ ጥቃት ለስደት፣ ለመፈናቀልና ለሞት ሲዳረጉ እንደ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ከጎን ሆኖ የሚያጽናና፣ አይዞአችሁ ብሎ የሚያበረታታ ያስፈልጋል፡፡ ነፍስን ለመታደግ አስፈላጊውን ሰብአዊ ርዳታ ለማድረግ እጃችንን መዘርጋት ከእኛ ከክርስቲያኖች ይጠበቃል፡፡ ምክንያቱም እኛ ክርስቲያኖች የተጎዱትን ለማየት የእግዚአብሔር ዓይን፤ የተራቡትን ለማጉረስ

የእግዚአብሔር እጅ፤ ለተሰደዱት ለማዘን የእግዚአብሔር ልብ ነንና ሊታሰብበት ይገባል፡፡

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በደብረ ዘይት ስለ ዳግም ምጽአቱ በተናገረበት አንቀጽ ‹‹ተርቤ አይታችሁ አላበላችሁኝም፣ተጠምቼ አይታችሁ አላጠጣችሁኝም፣ ታርዤ አይታችሁ አላለበሳችሁኝም›› ማቴ ፳፭ በማለት የተናገረው አምላካዊ ቃል እኛን የሚመለከት የማይመስለን ብዙዎች ነን፡፡

ትናንት ባለቤት የነበሩ ኢትዮጵያውያን ይልቁንም ኦርቶዶክሳውያን ወገኖቻችን ለረኀብ ለስደት፣ ለእንግልት እና ለሞት ሲዳረጉ ቢቻል የሚደረገውን ግፍና ጭቆና በመቃወም ከፊት መቆም ፤አጋር መሆንም ተገቢ ነው፡፡ ስደተኞችን በመቀበል የሚታወቁት ኢትዮጵያውያን ይልቁንም ክርስቲያኖች የክርስትናው ትርጉም ሲዛባብን እንደማየት የከፋ ነገር የለም፡፡ ለዓለም የምትተርፈው ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንዴት ለገዛ ምእመናንዋ (አማኞችዋ) መሆን ያቅታታል? የመጀመሪያዎቹን ክርስቲያኖች ያበዛው፤ እንደ መልካም መዓዛ ሆኖ ለብዙዎች የተዳረሰው ‹‹ ከእነርሱም አንድ ስንኳ ችግረኛ አልነበረም፤ ቤትና መሬት ያላቸውም ሁሉ እየሸጡ ገንዘቡን ያመጡ ነበር፡፡ አምጥተውም በሐዋርያት እግር አጠገብ ያኖሩት ነበር፤ እነርሱም ለእያንዳንዱ እንደፍላጎቱ ያካፍሉት ነበር፡፡›› ሐዋ.ሥ ፬ ፥ ፴፬-፴፭ በሚለው ቃል ብቻ ሳይሆን በተግባር የተገለጠው ክርስትና ዛሬ በእኛ ቸልተኝነት ጥያቄ ምልክት ውስጥ ነውና በእምነት ውስጥ ነን የምንል ሁሉ አጥብቀን ልናስብበት ይገባል፡፡

ዛሬ ተደጋግፈን ያላቆምነው ወገናችንን ነገ አናገኘውምና ትኩረት ሰጥቶ መሥራት አስፈላጊ ነው፡፡ ዛሬ ያልተቆረቆርንላት ቤተ ክርስቲያን ፈርሳ እንድታልቅ ዝም ማለት ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ከታሪክ መዝገብ ለማጥፋት በሚደረገው ስውር ዘመቻ ውስጥ ተሳታፊ መሆናችንን መዘንጋት የለብንም፡፡

ቤተ ክርስቲያን ዛሬ በውስጥም ሆነ በውጭ ባሉ ፈርጣማ ጡንቻዎች እና መዳፎች ስትደቆስ ‹‹ለምን?›› የማይል የቤተ ክርስቲያን ልጅ ወደዚህ ዓለም የመጣበትን እንዲሁም ክርስትናው ከእርሱ የሚጠብቀውን ሥራ እየሠራ አይደለምና አጥብቆ ሁሉም ራሱን መፈተሽ ይገባዋል፡፡ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ዛሬ ዘርፈ ብዙ ፈተናዎችን እየተጋፈጠች ትገኛለች፡፡ ይህንን ዘርፈ ብዙ ፈተና ልጆችዋ ተረዳድተው ከላይዋ ላይ ካላነሱላት፣ ወይም እንደ ሙሴ እጆችዋን መደገፍ ካልቻሉ ነገ የኔ የሚሉት ቤተ ክርስቲያንም ሆነ ምእመን ማግኘት ይቸግራልና በገዛ ሀገር ስደተኛ ከመሆን በፊት ዛሬ ላይ ቆም ብሎ መሥራት አስፈላጊ ነው፡፡

የቤተ ክርስቲያን ልጆች ዛሬ እየተገፉ እና እየሞቱ እንዲሁም በረኃብ በእርዛት እየተሠቃዩ ባሉበት አስቸጋሪ ወቅት አለንላችሁ ማለት የክርስቲያን ዋንኛ አላማ መሆን አለበት፡፡ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለተራቡት እንመጸውት ዘንድ እጆቹን አውሶናል፤ ድኃውን እናይ ዘንድ ዓይኖቹን ሰጥቶናል ፤ለተበደሉት እንራራ ዘንድ አዝዞናል፡፡ የክርስቶስ አምባሳደር ሆነን በተሾምንበት ሁሉ አውቀን እንተጋ ዘንድ ዘመኑ ከኛ ከክርስቲያኖች የሚፈልገው ዐቢይ ጥያቄ ነው፡፡

# ዛሬም ያላቆመው የዐደባባይ በዓላትን ዒላማ ያደረገ ትንኮሳ

*በካሣሁን ለምለሙ*

ከተወሰኑ ዓመታት ወዲህ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የምታከብራቸው የዐደባባይ በዓላት በሥርዓት እንዳይከበሩ፣ ኦርቶዶክሳውያን ምእመናን ሆኑ የቤተ ክርስቲያን አባቶች በሰላም ወጥተው በሰላም እንዳይገቡ ዘርፈ ብዙ ትንኮሳዎች ሲደርስባቸው ቆይቷል:: በምእመናንና በአባቶች ካህናት እንዲሁም ከተለያዩ ሀገራት በሚመጡ የውጭ ሀገር ጎብኚዎች ታጅበው የሚከበሩት እነዚህ የዐደባባይ በዓላት የተጋረጠባቸው የፀጥታ ስጋት ከዓመት ዓመት ሲጨምር እንጂ ሲቀንስ አልታየም::

የትንኮሳውን ዓይነትና ቦታን በመቀያየር ኦርቶዶክሳውያንን የማሳቀቅ፣ ስጋት ውስጥ የመክተትና ክብረ በዓላቸውን በሰላም እንዳያከናውኑ የማጨናገፍ ሴራ ከዕለት ዕለት እየጨመረ፣ ጡንቻውን እያፈረጠመ እዚህ ደርሷል:: በአንዳንድ አካባቢዎች በፀጥታ ኃይሎች ጣልቃ ገብነት ለማክበር ቢሞከርም በተወሰኑት አካባቢዎች ደግሞ ምንም ዓይነት ከልካይና ሃይ ባይ ባለመኖሩ(ቢኖርም የይስሙላ በመሆኑ) ምእመናን በገዛ ሀገራቸው ላይ ሃይማኖታቸውን በነፃነት እንዳያካሄዱ ተገደዋል:: በዚህ ዓመት ብቻ እንኳ በመስቀል እና በጥምቀት በዓላት ላይ ከመከበራቸው በፊት እየተከበሩ እና ከተከበሩ በኋላ የተፈፀሙት ፀረ ኦርቶዶክሳውያን ትንኮሳዎች በከተማውም ሆነ በገጠሩ ጥቂት የማይባሉ ነበሩ::

የመስቀልም ሆነ የጥምቀት በዓል በመጣ ቁጥር ለትንኮሳ የሚዘጋጁ ፀረ ኦርቶዶክሳውያን ኃይሎች በርካቶች ናቸው:: ከእነዚህ ተንኳሽና ዕረፍት የለሽ ፀረ ኦርቶዶክሳውያን ኃይሎች መካከል አክራሪ እስላሞች በቀዳሚነት ተጠቃሾች ናቸው:: እነዚህ አክራሪ እስላሞች በርከት ብለው በሚገኙባቸው አንዳንድ የሀገራችን ክፍሎች ሁሉ የዐደባባይ በዓላቱ የሚከበሩበትን ወቅት ጠብቀው በውኃ ቀጠነ በዓሉን ሊያውኩ ይችላል የሚሉትን ተግባር ሁሉ ይፈጽማሉ:: ሲያሻቸው "ታቦት ይዛችሁ በእኛ አካባቢ አትለፉ" ወይም ደግሞ ‹‹ሰንደቅ ዓላማ አትስቀሉ››፤ ‹‹አረንጓዴ፣ ቢጫና ቀይ ቀለም ያለበት ልብስ አትልበሱ››ይላሉ:: የዚህ ሁሉ መዳረሻው ወይም የጥቃቱ ምክንያት "ኦርቶዶክስ ክርስቲያን ለምን ሆናችሁ?" የሚል ሆኖ እናገኘዋለን:: ‹‹ለምን የእኛን ሃይማኖት አልመሰላችሁም›› የሚል ፍላጎት እንዳለበትም ከድርጊታቸው መረዳት እንችላለን::

ዐይን ያወጣውን የአክራሪዎች የወንጀል ድርጊት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የሚያስተካክል የፀጥታ ኃይል ባለመኖሩም ጥቃቱ በማን አለብኝነት በተደጋጋሚ ይፈጸማል:: የፀጥታ ኃይሎች በየአካባቢው ቢኖሩም ለሚከተሉት ሃይማኖት ያደሉ ወይም ለእውነት ያልቆሙ በመሆናቸው ችግሩን ለመፍታት አይሞክሩም፤ ለክርስቲያኖች በደልና እንግልትም አይጨነቁም:: ዘንድሮ ማለትም ጥር ፲፩ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም የተከበረው የጥምቀት በዓል እንደቀደመው ጊዜ ሁሉ በፀጥታ ችግር ውስጥ ማለፉ አልቀረም:: በተለይም በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ሀላባ ዞን ሀላባ ቁሊቶ ከተማ በጥምቀትና በቃና ዘገሊላ ዕለት የአካባቢው አክራሪ እስላሞች በበዓሉ ተሳታፊ ምእመናንና አገልጋዮች ላይ ከፍተኛ የሆነ ጥቃት ፈጽመዋል:: በዚህ ጥቃትም ምእመናንና አገልጋዮች መለስተኛና ከፍተኛ የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል:: እኛም በጉዳዩ ዙሪያ የአካባቢው የሃይማኖት አባቶችንና የመንግሥት አካላትን በስልክ አነጋግረናል::

የከምባታ፣ ጠንባሮና ሀላባ ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ ቆሞስ አባ ሚካኤል ታደሰ ለዝግጅት ክፍላችን በስልክ በሰጡት መረጃ "የእመቤታችንና የገብርኤል ታቦታት ከባህረ ጥምቀት ቦታቸው ተነሥተው ወደ መንበራቸው ሲመለሱ መስጅድ ውስጥ የነበሩ በርካታ አክራሪ

ሙስሊሞች በምእመናንና በታቦታቱ ላይ በድንጋይ ጥቃት ፈጽመዋል ብለዋል። በወቅቱ በዓሉን በማክበር ላይ የነበሩ ምእመናን ችግር ይኖራል ብለው ባለመጠርጠራቸው መለስተኛና ከፍተኛ የሆነ የአካል ጉዳት እንደደረሰባቸው ሥራ አስኪያጁ ተናግረዋል።

የአካባቢው አክራሪ እስላሞች ‹‹ታቦታቱን በአካባቢያችን አናሳልፍም›› ከማለታቸው ባሻገር በታቦታቱና በምእመናን ላይ ከፍተኛ የሆነ የድንጋይ ናዳ በማውረድ ጉዳት አድርሰዋል። ወደ ፌዴራልና ክልል መንግሥታት ስልክ ተደውሎ የፌዴራል ፖሊስ፣ መከላከያና የክልሉ ልዩ ኃይል ደርሰው ካረጋጉ በኋላ ሕዝበ ክርስቲያኑ በከፍተኛ ቁጭት፣ ለቅሶና ኀዘን ሆነው ታቦታቱን ወደ መንበረ ክብራቸው እንደሸኙ ሥራ አስኪያጁ አስረድተዋል። በወቅቱ በአካባቢው የነበሩት የፀጥታ አካላት ቁጥራቸው አነስተኛ ከመሆኑም ባሻገር መሣሪያ ሳይሆን ዱላ ብቻ የያዙ በመሆናቸው ሕዝበ ክርስቲያኑን ከጥቃት የመከላከልም የመጠበቅ አቅምም ሆነ ፍላጎት አልነበራቸውም ብለዋል። ይባስ ብለው አብዛኛዎቹ የፀጥታ አካላት በምእመናንና በታቦታቱ ላይ ይደርስ የነበረውን ጥቃት በታዛቢነት ይመለከቱ ነበር።

እነዚህ የፀጥታ አካላት አልፎ አልፎ ይህን እኩይ ተግባር ይፈጽሙ ከነበሩት አካላት ጋር በመወገን በሕዝበ ክርስቲያኑ ላይ ጥቃት ይፈጽሙ እንደነበርም ተናግረዋል። አንዳንድ የአካባቢው የፀጥታ ኃይሎች ደግሞ ጥቃቱን እንዲያስቆሙ ሲጠየቁ ‹‹ትእዛዝ አልተሰጠንም›› የሚል መሠረተ ቢስ ምክንያት ያቀርቡ እንደነበር የገለጹ ሲሆን ቤተ ክርስቲያን በየዓመቱ የጥምቀትና የመስቀል በዓላትን በዐደባባይ እንደምታከብር እየታወቀ ልዩ ጥበቃ አለመደረጉ ለፀረ ኦርቶዶክሳውያን ኃይሎች ጥቃት ተጋላጭ አድርጎናል ብለዋል።

ሥራ አስኪያጁ አክለውም የአካባቢው አክራሪ እስላሞች ከዚህ ቀደም ማለትም በ፳፻፬ ዓ.ም በተመሳሳይ ወቅትና ቦታ በታቦታትና በሕዝበ ክርስቲያኑ ላይ ከፍተኛ ጥቃት የፈጸሙ ቢሆንም የዘንድሮው ግን ከዚያ የተለየና የባሰ መሆኑን ገልጸዋል። አክራሪ እስላሞች ከዚህ ቀደም በተለያየ ወቅት አብያተ ክርስቲያናትን ለማቃጠል ጥረት ሲያደርጉ ቢቆዩም ኦርቶዶክሳውያን ወጣቶች ባደረጉት ተጋድሎ ሳይሳካላቸው ቀርቷል። የዘንድሮው ጥቃት የሚለየው ቁጥራቸው ከሦስት መቶ እስከ አራት መቶ የሚሆኑ አክራሪ እስላሞች ከገጠር ተሰባስበው በመምጣት ‹‹መስጅድ ተቃጠለ›› በሚል ሰበብ በሕዝበ ክርስቲያኑና በታቦታት ላይ ጥቃት መፈጸማቸው ነው ብለዋል። ካደረሱት የድንጋይ ጥቃት በተጨማሪ አብያተ ክርስቲያናትን ለማቃጠልና የባሕረ ጥምቀቱን የግንብ አጥር ለማፍረስ ጥረት ሲያደርጉም ቆይተዋል ብለዋል።

የአካባቢው የፀጥታ ኃይልም መስጅድ ውስጥ ሆነው በሕዝበ ክርስቲያኑና በታቦታቱ ላይ በድንጋይ ጥቃት ሲፈጽሙ የዋሉትን ትተው በቦታው ያልነበሩና በሁከቱ ያልተሳተፉ ኦርቶዶክሳውያን ወጣቶችን ለእስር እንደዳረጓቸው ሥራ አስኪያጁ አስረድተው ቤተ ክርስቲያን ወጣቶቹ ለምን እንደታሠሩባት ስትጠይቅም ‹‹አጣርተን እንለቃቸዋለን›› የሚል መልስ መስጠታቸውን ገልጸዋል ። በሀላባ ቁሊቶ ከተማ ያሉ አንዳንድ የመንግሥት አካላት ለሚከተሉት እምነት ያደሩ መሆናቸውን በመግለጽ እንዲህ ዓይነቱ ተግባር በክልሉ መንግሥት በኩል ውሳኔ እንዲያገኝ ሀገረ ስብከቱ ጠይቋል ብለዋል።

በሀላባ ቁሊቶ ከተማ የሦስቱ አድባራት ዋና አስተዳዳሪ መልአከ ኃይል ቆሞስ አባ ብርሃነ መስቀል በበኩላቸው ጥር ፲ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም በሀላባ ቁሊቶ ከተማ በሚገኝ ዐደባባይ አቅራቢያ ባለ መስጂድ ውስጥ የነበሩ በርካታ አክራሪ እስላሞች በምእመናንና በታቦታቱ ላይ ጥቃት እንደፈጸሙ ተናግረዋል። በወቅቱ በድንገት በተፈጠረው ችግር ምእመናንና አባቶች እንደተደናገጡ ያስረዱት አስተዳዳሪው በዕለቱ ከፍተኛ የሆነ የመሣሪያ ድምፅ ስለነበረ የቅዱስ ገብርኤልን ጽላት ይዘን በቅርብ ትገኝ ወደነበረችው የእመቤታችን ቤተ ክርስቲያን አስገብተናል ብለዋል። አክራሪ እስላሞች በፈጸሙት በዚህ ጥቃትም አራት ኦርቶዶክሳውያን ምእመናን የተጎዱ ሲሆን የአንደኛው ጉዳት ከፍተኛ በመሆኑ ለተሻለ ሕክምና ወደ ሐዋሳ ሆስፒታል እንደተላከ አስተዳዳሪው አስረድተዋል። የጥምቀትና የቃና ዘገሊላ በዓላት ካለፉ በኋላ የአካባቢው የፀጥታ ኃይላት ኦርቶዶክሳዊ ወጣቶችን እያደኑ ያለምንም ጥፋታቸው አስረዋል። ወጣቶቹ በበዓለ ጥምቀትም ሆነ

በቃና ዘገሊላ ዕለት ችግሮች በሰላማዊ መንገድ እንዲፈቱ ጥረት ሲያደርጉ ነበር ያሉት አስተዳዳሪው መስጅድ ውስጥ ሆነው በሕዝበ ክርስቲያኑና በታቦታቱ ላይ የድንጋይ ናዳ ሲያወርዱ የነበሩ አክራሪ እስላሞች ግን አንዳቸው እንኳን አለመታሰራቸውን ገልጸዋል።

አክራሪዎቹ ይፈጽሙት ለነበረው ጥቃት የአጸፋ ርምጃ ባልወሰዱ ኦርቶዶክሳውያን ወጣቶች ላይ ፍትሐዊ ያልሆነ የእስር ርምጃ መውሰድ የሰብአዊ መብት ጥሰት እንደሆነ አስተዳዳሪው ተናግረው አንድ የሰበካ ጉባኤ አባልን ጨምሮ አስራ ሰባት ኦርቶዶክሳውያን ያለምንም ወንጀል በእስር ላይ ይገኛሉ ብለዋል። እነዚህ የታሰሩ ወጣቶች በተለይ ቤተ ክርስቲያንን መኪና ከማቅረብ ጀምሮ በሁሉም ነገር እገዛ ሲያደርጉ የነበሩና ሌሎችም በበዓለ ጥምቀት ወቅት በቦታው ያልነበሩ እንደሆነ አስተዳዳሪው አስረድተዋል።

የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ሕርያቆስም ወጣቶቹ በታሰሩባቸው አካባቢዎች ተገኝተው ያጽናኑ ሲሆን ከመንግሥት አካላት ጋርም በጉዳዩ ዙሪያ ውይይት ማድረጋቸውን፤ ጉዳያቸው እየተጣራ ከእስር እንደሚፈቱ የመንግሥት አካላቱ እንዳሳወቋቸው ገልጸዋል። ብፁዕነታቸው በራሳቸው ዋስትናም ወጣቶቹ ከእስር እንዲፈቱ የአካባቢውን የመንግሥት አካላት መጠየቃቸውን እንዲሁም መንግሥት በሚፈልጋቸው ጊዜም ለማቅረብ ዝግጁ እንደሆኑ መናገራቸውን አስተዳዳሪው አክለዋል። ይሁን እንጂ ወጣቶቹ እስካሁን ድረስ ከእስር እንዳልተፈቱ አስታውቀዋል። ቤተ ክርስቲያን ወጣቶቹ ከእስር እንዲፈቱ ተግታ እንደምትሠራና ከዚህ ቀደም እንደተደረገው ሁሉ ወጣቶች ተደራጅተው ራሳቸውንና ቤተ ክርስቲያናቸውን እንዲጠብቁ የማድረግ ሥራ እንደሚሠራ ተናግረዋል። በበዓለ ጥምቀት ወቅት አክራሪ እስላሞች የፈጸሙትን ጥቃት የአካባቢው የፀጥታ አካላት ድርጊቱን እንዳወገዙና እስልምናን የማይወክል ነገር ግን የአክራሪዎች ተግባር እንደሆነ መናገራቸውን አስተዳዳሪው አንሥተዋል።

የሀላባ ቁሊቶ ከተማ የሦስቱ አብያተ ክርስቲያናት የሰበካ ጉባኤ ም/ሰብሳቢ አቶ አድነው ወልዴ እንደተናገሩት ደግሞ በኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች ላይ የሚፈጸመው ትንኮሳ አሁን የተጀመረ እንዳልሆነ ገልጠው ከዚህ ቀደምም ብዙ ሃይማኖት ተኮር ትንኮሳዎች እንደነበሩ አስረድተዋል። ለዐደባባይ በዓላት ማክበሪያነት እንዲውል ፴፯ ሺህ ካሬ ሜትር ቦታ በሕጋዊ መንገድ ከተሰጠን በኋላ ቦታውን ማልማት ስንጀምር ለሚከተሉት ሃይማኖት ያደሩ የአካባቢው የመንግሥት ባለሥልጣናት ‹‹አታለሙም አቁሙ›› ብለው ከልክለውናል ሲሉ በአካባቢው እየተፈጸመ ያለውን በደል በማሳያነት አንሥተዋል።

የጥምቀት በዓል ከመድረሱ በፊት የፀጥታ ሥጋት እንዳለብን ለሀላባ ቁሊቶ ከተማ አስተዳዳር ልዩ ጥበቃ እንዲያደርግልን በደብዳቤ ያሳወቅን ቢሆንም ጥያቄያችን ችላ በመባሉ አክራሪ እስላሞች መስጅድ ውስጥ ሆነው ጥቃት ፈጽመውብናል ብለዋል። አንዳንድ የአካባቢው የመንግሥት አካላት ለአክራሪዎች እኩይ ተግባር የተገዙ በመሆናቸው ጥቃት ሲፈጸምብን በቸልታ ከማየት ባሻገር ቤተ ክርስቲያን መብቷን ስትጠይቅ እንዳይፈጸምላት የሚሠሩ እንደሆኑ አስረድተዋል።

**የትንኮሳውን ዓይነትና ቦታን በመቀያየር ኦርቶዶክሳውያንን የማሳቀቅ፣ ስጋት ውስጥ የመክተትና ክብረ በዓላቸውን በሰላም እንዳያከናውኑ የማጨናገፍ ሴራ ከዕለት ዕለት እየጨመረ፣ ጡንቻውን እያፈረጠመ እዚህ ደርሷል።**

ለሀላባ ዞን ፖሊስ መምሪያ (ኢ/ር ታረቀኝ ጉራች)፣ ለሀላባ ዞን ዋና አስተዳዳሪ (ዶ/ር መሐመድ ኑርዬ)፣ ለሀላባ ዞን ሰላምና ፀጥታ መምሪያ ኃላፊ (አቶ ሱሌይመን ሀሰን)፣ ለሀላባ ዞን ፍትህ መምሪያ ኃላፊ (አቶ አብዱቃልድር ሎላሽ) እንዲሁም ለሀላባ ቁሊቶ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ (አቶ ሀሩና አህመድ) ስልክ ደውለን መረጃ ለመጠየቅ ጥረት ብናደርግም የተወሰኑት የመንግሥት አካላት ስልክ አንሥተው መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ ያለመሆናቸውን የገለጡ ሲሆን ሌሎች ደግሞ ስልክ ሊያነሱልን ባለመቻላቸው ምላሻቸውን በዚህ ጽሑፍ ማካተት አለተቻለም።

# «የእግዚአብሔር ኃይልና ጥበብ ነው ያኖረኝ»

***መጋቤ ሐዲስ መምህር አባ አእምሮ ብሩ***

***ክፍል ሁለት***



መጋቤ ሐዲስ መምህር አባ አእምሮ ብሩ

**በመጽሐፈ ሲራክ**

***የተወደዳችሁ አንባብያን የዚህን ጽሑፍ የመጀመሪያ ክፍል ከዚህ በፊት በነበረው እትም ላይ ማቅረባችን ይታወሳል። ቀጣዩንና የመጨረሻውን ክፍል ደግሞ እንደሚከተለው አቅርበነዋል።***

ናዝሬት ቅድስት ማርያም በመጽሐፍ መምህርነት ተመድቤ ብሔድም የሰብከተ ወንጌል ኃላፊነቱንም ደርበው ስለሰጡኝ ሁለቱም የሥራ መደብ ላይ አገለግል ነበር። ሠርክ ጉባኤ ከእሑድ እስከ እሑድ አስተምር ነበር፤ ከጉባኤው በኋላ ማታ ማታ ልጆች ሰብስቤ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ድረስ ሥርዓተ ቅዳሴ አስተምራለሁ፤ በእርግጥ ብዙ ዲያቆናትም ወጥተዋል። እዚያ ካስማርሁዋቸው ውስጥ ውጪም ሄደው የሚያገለግሉ አሉ። ያኔ ብዙውን ሥራ ካለ አንድ ረዳት የምሠራው እኔ ነበርኩ። መምህር ዘላለም ወንድሙ ከወር አንድ ቀን ቅዳሜ ወይም እሑድ እየመጣ በስብከተ ወንጌል ትምህርት ያግዘኝ ነበር እንጂ ሌላ የሚያግዘኝ ሰው አልነበረም። በዚያ የሥራ ብዛት ዕረፍት ስላልነበረኝ ሰውነቴ እጅግ ተጎድቶ ነበር። ለአራት አመታት በዚያ ካገለገልኩ በኋላ በ፲፱፻፹፰ ዓ.ም ዝውውር ጠይቄ በመጽሐፍ መምህርነት ወደ ደብረ መዊዕ ቅዱስ ሚካኤል ካቴድራል መጣሁ። እንግዲህ ከ፲፱፻፹፰ ዓ.ም ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ እዚህ ነው ያለሁት።

***ስምዐ ጽድቅ፦*** አሁን እዚህ ከመጡ በኋላ በመጽሐፍ መምህርነት ቀጠሉ ማለት ነው? የምን ያህል ተማሪዎች አሉዎት?

***አባ አእምሮ ፦*** ወደ ደብረ መዊዕ ቅዱስ ሚካኤል ካቴድራል ተዛውሬ ስመጣ በመጽሐፍ መምህርነት ቢሆንም ብዙ ተማሪ ግን አልነበረም። እንደመጣሁ አካባቢ መጽሐፍ መምህርነት ጀምሬ ነበረ ፤አንድ አራት ልጆች መጥተው መማር እንደጀመሩ የሚበላ የለም፣ የማስተማሪያ ቤት የለም ማንም ዞር ብሎ የሚያያቸውና የሚረዳቸው በማጣታቸው ተማሪዎቹ ጥለውት ሄዱ። እነዚህን ልጆች ቤተ ክርስቲያን መጠለያ እንኳ ብትሰጣቸው ለምግባቸው የአዲስ አበባ ሕዝብ ደግ ነው ለምነው ይማሩ ነበር፤ ሆኖም የሚያስተባብር በመጥፋቱ ትምህርቱን አቋርጠው ጥለውት ሄደዋል። ከዚያ ወዲህ ምንም ተማሪ የለም። የመጽሐፍ መምህርነቱ በዚህ ምክንያት ከመቆሙ ውጪ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በተለይ በስብከተ ወንጌል ሳገለግል ነው የቆየሁት አሁንም እያገለገልኩ ነው።

ሌላው ወደ ደብረ መዊዕ እንደመጣሁ በቦታው ላይ ፊደል የሚያስቆጥር መምህር አልነበረም፤ እኔም ዝም ብዬ ከምቀመጥ ለምን ልጆችን ፊደል አላስቆጥርም?

ብዬ በራሴ ፍላጎት እና መነሣሣት ማስማስተማር ስጀምር ብዙ የአካባቢው ልጆች መጡ። ግእዙን፣ ውዳሴ ማርያሙን፣ ንባቡን፣ ዳዊቱን ሁሉ አስተምራለሁ። ማታ ማታ መጠለያው እና አዳራሹን ሞልተው ነው ሕፃናቱ የሚማሩት። አሁን ዓለማዊው ትምህርት በፈረቃ ስለሚሰጥ ትምህርት በሌላቸው ቀን እየመጡ ጥዋት እስከ ስድስት ሰዓት እና ማታ ከአስራ ሁለት ሰዓት እስከ አንድ ሰዓት ይማራሉ፤ ሆኖም ብቻዬን ነው የማስተምራቸው አጋዥም የለኝም።

ከማስተምራቸው ውስጥ ከፊደል ጀምረው፣ ዳዊት ዘልቀው ውዳሴ ማርያም፣ መልካ መልኩን ሁሉ የጨረሱ አሉ። መጀመሪያ መልእክተ ዮሐንስን ግእዝና ወርድ ንባቡን አስነብባቸዋለሁ እሱን ካነበቡ በኋላ ወንጌለ ዮሐንስን ቀጥሎ ዳዊትን አስነብባቸዋለሁ። ከዚህ በፊት ግን በስመ አብ ብለው ጀምረው ውዳሴ ማርያም አንቀጸ ብርሃን፣ መልካ መልኮቹን እነዚህን ጨርሰው ነው ወደ ምንባብ የማመጣቸው።

ሂደቱ እንደዚህ ነው በዚህ መካከል ይህን ሁሉ ጨርሰው ዳዊት የሚማሩ ጎበዝ ሴቶች ልጆች አሉ፤ ዳዊቱን ጨርሰውም አጠናቀው የሄዱ አሉ። አሁንም በጣም ጎበዝ የሆኑ ሴቶች ልጆች አሉ። የወንጌሉን ንባብ ጨርሰው ወደ ዳዊት የሚገቡ ማለት ነው። ወንጌል ከጨረሱ በኋላ ዜማ የሚፈልግ ካለ ወደ ዜማ ቤት፣ ቅዳሴ የሚፈልግ ወደ ቅዳሴ ቤት ይሄዳሉ። ቅዳሴ ቤት የገቡ ብዙዎች ናቸው ቅዳሴውን ጨርሰው አሁን ቤተ ክርስቲያን የሚያገለግሉ ብዙ ልጆች ናቸው። እስከዛሬ እየተማሩ የሄዱ በቁጥር ይህን ያህል ናቸው ብዬ መናገር ባልችልም ብዙ ዲያቆናት እየተማሩ ዲቁና እየተቀበሉ ሄደዋል። እዚህም በተራ እየገቡ የሚቀድሱ ዲያቆናት ብዙ ናቸው። ዳዊት፣ ውዳሴ ማርያም ንባብ የሚማሩ አሁንም ሞልተዋል።

***ስምዐ ጽድቅ ፦*** እርስዎ ያፈሩዋቸው ተማሪዎች ምን ያህል አሉ ለምሳሌ በቤተ ክርስቲያናችን የተለያዩ መዋቅሮች ላይ ካሉ ቢነግሩን?

***አባ እጅምሮ፦*** በእርግጥ ካስተማርኳቸው ተማሪዎች እልቅና ላይ የደረሰ ሰው የለም፤ ናዝሬት እያለሁ ካስተማርኳቸው ውስጥ አሁን በቤተ ክርስቲያን በአገልግሎት ላይ የሚገኙ አሉ። ቅድም እንደነገርኩሽ እዚህ ከመጣሁም መጽሐፍ የሚማር ተማሪ ባለመኖሩ ንባቡን ዳዊቱን ይህንን መልካ መልኩን እሱን እሱን ነው የማስተምር እነዚህ ብዙ ናቸው። በደሞዝም የተቀጠሩ በአብዛኛው በዲቁናና በቅስና አገልግሎት ላይ ነው ያሉት።

***ስምዐ ጽድቅ፦*** በዚሁ በደብረ መዊዕ ቅዱስ ሚካኤል ካቴድራል በሰብከተ ወንጌል፣ የኮሌጅ እና የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን፣ የተለያዩ ማኅበራትን እና ምእመናን ያስተምሩ እንደነበር ይነገራል እስኪ ስለዚያ ይንገሩኝ?

***አባ እጅምሮ፦*** እውነት ነው በሰብከተ ወንጌል፣ በአካባቢው ላይ ያሉ የኮሌጅ፣ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች እንዲሁም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሠራተኞችንና የተለያዩ ማኅበራትን ሰብስቤ ስብአስተምራለሁ። ለምሳሌ ማኅበረ ቅዱሳን ሰብስቧቸው በዚህ ግቢ የሚማሩ የቅዱስ ጳውሎስ የጤና ተማሪዎች ነበሩ። ከነዚህ ተማሪዎች ጋር ያሳለፍኩት ጊዜ በጣም ነው የሚስደስተኝ። ጉባኤውን በጸሎት ማስጀመርና ሲያልቅ በጸሎት በመዝጋት እንዲሁም መምህር በሚቀርበት ጊዜ ሽፍኜ በማስተማር ማኅበሩን አግዝ ነበር። ታላላቆቹ የማኅበረ ቅዱሳን አባላትም ለማስተማር ይመጡ ነበር።

በየዓመቱ ትምህርታቸውን ሲጨርሱ እናስመርቃቸው ነበር ፊት የመጣው ይመረቃል ከኋላ የመጣው ደግሞ ይቀጥላል። በኋላ ላይም የማይክሮ ሊንክ ኮሌጅ ተከፍቶ ስለነበር እነሱንም በዚሁ ግቢ ውስጥ ሰብስቤ ስብከተ ወንጌል አስተምር ነበር። ብዙ ተማሪዎች ከዚህ ቦታ መንፈሳዊ ትምህርት ቀስመው ሄደዋል። ያን ጊዜ አዳራሹ ስለሚጠበን ውጭ ላይ ድምጽ ማጉያ በመጠቀም ነበር የምናስተምራቸው። ይህ ጉባኤ እስካሁን ድረስ አለ እሱን ጉባኤ እኔው ነኝ የምከታተለው።

ከነዚህ የግቢ ጉባኤ ተማሪዎች በተጨማሪ ቤተ ማርያም፣ ቤተ ሚካኤል፣ ቤተ ጊዮርጊስ፣ ማኅበረ አዳም ወሔዋን የሚባሉ አራት ማኅበራትን በዚሁ ግቢ ውስጥ ሰብስቤ ስብከተ ወንጌል የማስተምራቸው እኔ ነበርኩ። እነዚህ ማኅበራት ከጉራጌ ማኅበረሰብ የመጡ ነበሩ፤ ከሚማሩት መንፈሳዊ ትምህርት ባሻገር የተጎዱ አብያተ ክርስቲያናትን ያሳድሳሉ፣ አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናትን ያሳንጻሉ። ገጠሩ ላይ ክርስቲያኖች በአካባቢያቸው ምእመናን አስከሬን የሚቀብሩበት አጥተው ቤተ ክርስቲያን እና መቃብር ፍለጋ የስድስት ሰዓት መንገድ የሚጓዙበት ጊዜም ነበረ፤ እነዚህ ማኅበራት እንዲህ ዓይነት ችግር ባሉባቸው ቦታዎች በመሄድ አብያተ ክርስቲያናትን በቅርባቸው አሳንጸውላቸዋል። ይህን ሁሉ ያደረጉት እዚህ መጥተው ወንጌል በመማራቸው ነው። የእነርሱ ጥቅም ዘርፈ ብዙ ነው ማለት ይቻላል።

**ትምህርት ቤት ሳለን አንዲት ቁምጣና አንሶላ ነበረ ልብሳችን ሌላ የለም፤ ያችኑ ቀን ለብሰን እንውላለን ሌሊት ለብሰናት እናድራለን። ይህችው ቁምጣ ከመቀመጫዬ ላይ አለቀችብኝ ምን ላድርግ? ገንዘብ የለኝ አልገዛ፤ በቅርብ ዘመድ የለኝ አልብሱኝ አልል።**

ሌላው ማኅበረ ቅዱሳን ወደዚህ ካቴድራል በመምጣት እና ፈቃድ በመውሰድ በአካባቢው ላሉ የመንግስት ሰራተኞች መንፈሳዊ ትምህርት ይሰጥ ነበር። የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል፣ የፓስተር ኢንስቲዩት፣ የጤና ጣቢያ፣ የመድኃኒት ፋብሪካ፣ የመናኸሪያ ሰራተኞችን ዓርብ ዓርብ አስተምር ነበር። ለነዚህ ሁሉ አገልግሎቶች የደብሩ ሰበካ ጉባኤ ደብዳቤ ሰጥቶኝ ነው እያገለገልኩ ያለሁት። ብዙ ሰራተኞች እየመጡ ይማሩ ነበር፤ አዳራሹ እየሞላ ውጭ ቆመው የሚማሩ ነበሩ።

***ስምዐ ጽድቅ፦*** አሁን ጉባኤው እንዴት እየሄደ ነው?

***አባ እጅምሮ፦*** አሁን እንኳ በኮረና ምክንያት አገልግሎቱ ቆሞ ነበር በዚህ ሰሞን ጀምረናል አገልግሎቱ እየተሰጠ ነው። እዚህ ጤና ጣቢያው ላይ የማኅበረ ቅዱሳን ልጆች አሉ እነሱ ሌሎች ሰራተኞችን እየቀሰቀሱ ጉባኤው እንደበፊቱ ተጀምሯል።

***ስምዐ ጽድቅ፦*** እንደ እርስዎ ያሉ መምህራን እንዲበዙ ቤተ ክርስቲያን ምን ማድረግ አለባት ይላሉ?

***አባ እጅምሮ፦*** ቤተ ክርስቲያን ተተኪ መምህር እንዲበዛ ተግታ መሥራት አለባት እላለሁ፤ አሁን ግን ያ እየሆነ አይደለም። ይልቁንም ማኅበረ ቅዱሳን ገጠሩ ድረስ ዘልቆ እየሠራ ነው። ቤተ ክህነት፣ ባለ ሀብት የቤተ ክርስቲያን ልጆች፣ መንግሥት ለዚህ ስራ በኅብረት ቢሰሩ ጥሩ ነው እላለሁ። በተለይ ቤተ ክህነት አጥብቆ ሊያስብበት ይገባል። የአብነት መምህራኑ የታሉ ተብለው ተፈልገው ቦታ ሊሰጣቸው ይገባል። ያኔ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ተተኪ ትውልድን ያፈራሉ። ለዚህ ደግሞ ሁሉም ይተባበር ነው የምለው። ሁሉም የቤተ ክርስቲያን ልጆች አጥብቀው ሊያስቡበት ይገባል እላለሁ።

እኔም እኮ አሁን ቁጭ ብዬ የማስተምረው ዳቦ ስላገኘሁ ነው። እኛ ስንማር ደረቅ ባቄላ፣ ለምለም እንጀራ በልተን ነው እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እዚህ የደረስነው። የአብነት መምህራኑን እንደዚህ የሚያስቀጥል ሁኔታ አይደለም ዛሬ ያለው። ለዚህ ነው የአብነት መምህራኑ በደንብ ሊያዙ ይገባል የምለው። አሁን ማኅበሩ ብቻ ነው እየሠራ ያለው ለምሳሌ ጎንደር መንበረ መንግሥት አራቱ ጉባኤ ቤት ማለት ነው ተማሪው በጀት ወጥቶለት ስርኩ ኅብስት ተሰጥቶት ያው ያቺን እየበላ እየተማረ ነው። እንደ አገባባቸው የጊዜ ገደብም ተሰጥቶአቸው የተማረው ቦታ እየለቀቀ ያልተማረው እየገባ ነው ያለው፤ እንዲህ ቢሆን ብዙ ነገር ይሠራል። ነገር ግን እንዲህ ዓይነቱ ዕድል አንድና ሁለት ቦታ ነው ያለው ሌላ ቦታ የለም።

እንዲህም ሆኖ በገጠሩ ዓለም የእግዚአብሔር ሥራ ይገርማል። በደመወዝ ሳይሆን በረድኤተ እግዚአብሔር ተጠብቀው የሚያስተምሩ አባቶች ሞልተዋል።

***ስምዐ ጽድቅ፦*** ትምህርት ቤት እያሉ የመገልበጥ ሥራ ከሠሩባቸው መጻሕፍት ውጪ የጻፏቸው መጻሕፍት አሉ?

***አባ እእምሮ፦*** በዓይኔ ምክንያት መጽሐፍ ማዘጋጀት አልቻልኩም። እንኳን መጽሐፍ ልጽፍ የማነበውን እንኳ እየተቸገርኩ ነው ያለሁት። በጣም የሚገርመው እስከ እድሜ ልኬ ትምህርት አቆማለሁ የሚል እምነት አልነበረኝም። መሀከል ላይ ዓይኔ ታመመ አሁን አምስት ደቂቃ ሳነብ እንባዬ ነው የሚፈሰው። ተመርምሬው ነበር ዶክተሩ ዓይህ ስለተጎዳ ጥበቃ አድርግለት በማለት አሳስቦኛል። እንግዲህ በዓይኔ ምክንያት ምንም ነገር መሥራት አልቻልኩም ማለት ነው። በልጅነቴ ዓይኔ በመጎዳቱ አሁን ላይ ምንም መስራት አልቻልኩም። እንደውም ትምህርት ለመማር በጣም ተነሳስቼ ነበር ነገር ግን ዓይኔን እንዴት ላድርገው አልቻልኩም ትምህርቱን አቆምኩኝ።

***ስምዐ ጽድቅ፦*** በአገልግሎት ዘመንዎ ደስ የሚልዎት ወይም ያዘኑበት አጋጣሚ ካለ ገጠመኝዎትን ይግለጹልን?

***አባ እእምሮ፦*** በሕይወት ዘመን ጥሩም መጥፎም ነገር ይገጥማል። እኔ በሕይወቴ የተደሰትኩበት አጋጣሚ እስቴ መካነ ኢየሱስ እያለሁ አራቱን ወንጌላውያን ትርጓሜ በእጄ መገልበጤ ነው። ቀለም በጥብጬ ብዕር ቀርጬ ደብተር አስምሬ በመጻፌ ትዝ የሚለኝና የሚያስደስተኝ ትልቁ ሥራ እሱ ነው። ሌላው እዚህ ደብረ መዊዕ ከመጣሁ በኋላ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎችን እና የተለያዩ የቤተ ክርስቲያን ልጆችን በማስተማር ያሣለፍኩት ጊዜ ነው የሚያስደስተኝ፤ በእርግጥ አሁንም በዚሁ አገልግሎት ውስጥ ነው ያለሁት።

ሌላው በሕይወት ዘመኔ ክፉ አጋጣሚ ነው ብዬ የማነሳው የአብነት ት/ቤት የገጠመኝን ነው። በአብነት ት/ቤት ብዙ ፈተናዎችን አልፌአለሁ ማጣት፣መራብ፣መታረዝ ስንቱ ይዘረዘራል? በተለይ እስቴ መካነ የሱስ ብዙ አሳልፌያለሁ በእርግጥ ትልቅ እውቀት ይገኜ ወጥቻለሁ እሱ ነው ትልቁ ትርፌ የምለው። አሁን ላይ ሆኜ ሳስበው ያ ይመስለኛል ዛሬ ከሰው ፊት ያደረሰኝ። እንደዚያ የምንለብሰው፣ የምንበላው ሳይኖረን ቤተ ክርስቲያን እናገለግል ነበር። ሰዓታት፣ ማኅሌት እንቆም ነበር በፈቃዳችን ነው እንጂ ምንም አይከፈለንም። ከዚያ ህይወት የሚያስደስተው ያን ጊዜ የተሰጠን ጥንካሬና ብርታት ብቻ ነው። እንዴት ነው ሰው ምግብ ሳይበላ ውሃ ሳይጠጣ ቃለ እግዚአብሔርን እያገለገለ መኖር የሚችለው? ይህ የመላእክት ሥራ ነው እያልኩ አሁን ሳስበው ይገርመኛል።

ትምህርት ቤት ሳለን አንዲት ቁምጣና አንሶላ ነበረ ልብሳችን ሌላ የለም፤ ያችኑ ቀን ለብሰን እንውላለን ሌሊት ለብሰናት እናድራለን። ይህችው ቁምጣ ከመቀመጫዬ ላይ አለቀችብኝ ምን ላድርግ? ገንዘብ የለኝ አልገዛ፤ በቅርብ ዘመድ የለኝ አልብሱኝ አልል። አስታውሳለሁ አንድ ቀን ወደ ማታ ላይ ቁራሽ ልመና ወደ መንደር ስሄድ ከአንዱ ቤት ጓሮ ወይም ኮሲ ላይ ትልቅ ቡትቶ ተጥሏል ከዚያ ላይ ትልቅ ካኪ ተጥፎበት አየሁኝ። ያንን ቡትቶ ሰው እንዳያየኝ ይዤው ጫካ ገባሁና ካኪውን ከውስጡ አውጥቼ ከወንዝ ወስጄ በማጠብ ያንን ጥፌ የተወሰነ ጊዜ ተጠቀምኩበት። አሁን ሳስበው ይገርመኛል፤ እንባዬ ሁሉ ይመጣል። ‹‹ድህነት ከሰማይ ይርቃል የሚባለው ለካ እውነት ነው›› እላለሁ። ወይ እግዚአብሔር! ደሀውን ሀብታም፤ሀብታሙን ደሀ የምታደርገው ብዬ የነቢዩ ዳዊትን መዝሙር እያስታወስኩ አመሰግነዋለሁ። እንግዲህ ከዚያ ተነስቼ ነው ወደ ጎንደር ፤ከጎንደር ወደ ናዝሬት፤ ከናዝሬት እዚህ የደረስኩት። እዚህ የአዲስ አበባ ሕዝብ እንደሚታወቀው ነው ባልታሰበው ነገር ይመጣል ልብሱ፣ ጋቢው፣ ካባው ወደ ፲፩ ካባ ነው ለሰው የሰጠሁት። ይሄ ራሱ ታሪክ ነው። ለወደፊት የሚመጣውን አላውቅም እግዚአብሔር እስከዚህ ድረስ አድርሶኛል።

***ስምዐ ጽድቅ፦*** አባታችን ስለሰጡን ቃለ መጠይቅ በእግዚአብሔር ስም አመሰግናለን?

***አባ እእምሮ፦*** እኔም ፈልጋችሁ መጥታችሁ ካለኝ ጥቂት እንዳካፍል እንግዳ ስላደረጋችሁኝ እግዚአብሔር ይስጥልኝ።

# "የቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያ ሥራ መሆን ያለበት የልጆቿን ሰላምና ደኅንነት ማስጠበቅ ነው"

*-ብፁዕ አቡነ አብርሃም (የባሕር ዳር ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ)*

**ክፍል ሁለት**



*ብፁዕ አቡነ አብርሃም*
*(የባሕር ዳር ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ)*

*በካሣሁን ለምለሙ*

***የተወደዳችሁ አንባብያን የዚህን ጽሑፍ የመጀመሪያ ክፍል ከዚህ በፊት በነበረው እትም ላይ ማቅረባችን ይታወሳል። ቀጣዩንና የመጨረሻውን ክፍል ደግሞ እንደሚከተለው አቅርበነዋል።***

***ስምዐ ጽድቅ፡-*** የቤተ ክርስቲያን ጠላቶች በሕዝበ ክርስቲያኑ ላይ ጥፋት ሲያደርሱ እንደቆዩ ይታወቃል። ቤተ ክርስቲያን ጥፋቱ ከደረሰ በኋላ ጊዜያዊ ድጋፍ ከማድረግ ባሻገር ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት  በመንግሥት ላይ ጫና ማሳደር እንዴት አልቻለችም?

***ብፁዕ አቡነ አብርሃም፡-*** በመንግሥትም ሆነ በሌላ አካል ላይ ጫና አሳድሮ ችግሩን ለመፍታት ጥረት ከማድረግ በፊት የሚቀድመውን ማስቀደም መልካም ነው። ይኸውም መጀመሪያ በጽንፈኞች ጥቃት ችግር ላይ የወደቁ ምእመናን በተቻለን አቅም መረዳት፣ ከጎናቸው መሆናችንን ማሳየትና ሥነ ልቡናቸውን ማደስ ያስፈልጋል። ይህንን ካደረግን በኋላ ደግሞ ችግሩ በዘላቂነት የሚፈታበትንና ኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች እንደማንኛውም የሀገሪቱ ዜጋ ሰብአዊ መብታቸው ተከብሮላቸው እንዲኖሩ የሚያስችላቸውን ሥራ ከመንግሥትና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ሆኖ መሥራት ያስፈልጋል።

ሰላምን ከሌላ አካል ከመጠበቅ ደግሞ እኛ የቤተ ክርስቲያን ልጆች ተናበንና ተግባብተን መሥራት መቻል አለብን። መናበባችን ከመንበረ ፓትርያርክ እስከ አጥቢያና ምእመናን ድረስ የሚደርስ መሆን አለበት። ቤተ ክርስቲያን ከሠራችው ያልሠራችው ይበልጣልና የቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያ ሥራ መሆን ያለበት የልጆቿን ሰላምና ደኅንነት ማስጠበቅ ነው። እንዴት ማስጠበቅ አለባት ለሚለው የመጀመሪያው አምላኳን በጸሎት በመጠየቅና ከመንግሥትና ከሌሎች አካላት ጋር በጋራ በመሥራት ሊሆን ይገባል። በዚህ ዘመን በመንግሥት ላይም ሆነ በሚመለከተው አካል ላይ ጫና ተፈጥሮ ችግሮችን ማስተካከል ይቻላል ማለት ትንሽ ይከብዳል። ለአብነት በመተከል ዞን በንጹሓን ዜጎች ላይ የተፈጸመውን ጥቃት ለማስተካከል ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሳይቀር በቦታው ተገኝተው ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት አድርገው ነበር። ዳሩ ግን እርሳቸው ከተመለሱ በኋላ በርካታ ንጹሓን ወዲያው ተገድለዋል። ስለዚህ መንግሥትን የማይሰማ እንዲሁም እግዚአብሔርን የማይፈራ ትውልድ ምንም ጫና ብትፈጥር ከጥፋት ድርጊቱ አይመለስም።

እንደ ኦሪቱ ዘመን ያጠፋህን አጥፋው፣ የገደለህን ግደለው የሚሆን ከሆነ አያዛልቀንም፤ለሀገር አንድነትና ሰላምም የሚጠቅም አይደለም። ቤተ ክርስቲያን ሁሌም ሰላምን፣

አንድነትንና ፍቅርን ነው የምትሰብከው፤ ታጠቅ የገደለህን ግደል፤ ዝረፍ የሚል አስተምህሮም የላትም። ቤተ ክርስቲያን የትዕግሥት ቤት ናት፤ ትናትናም ክብሯን ጠብቃ ኖራለች፤ ዛሬም እየኖረች ነው፤ ነገም ለሀገር ጠቃሚና አሳቢ ሆና ትቆያለች። በሰዎች ላይ ጥፋት ስለሚያደርሱ ሰዎች ሁሉ ፈጣሪዋን ትለምናለች። ለጥፋት የተሰማሩ ኃይሎች ከጥፋታቸው እንዲመለሱና ለሰው አሳቢና የቀና ሕይወት እንዲመሩ ቤተ ክርስቲያን ሁሌም ትጸልያለች።

የሀገራችን የፖለቲካ ሁኔታ እጅግ እየተበላሸ መጥቷል። ለሀገርና ለወገን የማይጨነቁና የማያስቡ ፖለቲከኞች ተፈጥረው እየተመለከትን ነው። በሰው ሞት፣ ስደት፣ ስቃይና ችግር ሀብት ለማካበትና ሥልጣን ለመቆናጠጥ የሚያልሙ የፖለቲካ ሰዎች እየተበራከቱ መጥተዋል። ለወገን ደራሽ የመሆን ስሜት ያላቸው ሳይሆኑ አንዱን ጥሎ የማለፍ ሥሜት ያላቸው ሰው መሰል ግን አውሬ የሆኑ ፖለቲከኞች በየአካባቢው ተፈጥረዋል። በተለይ ለራሳቸው ዘውግና ሃይማኖት ብቻ የሚሠሩ በርካቶች ናቸው። ስለሆነም በሌላው ዘውግና ሃይማኖት ላይ ጫናና ጥቃት እንዲደርስ ሆነ ብለው እየሠሩ ያሉ በርካታ ፖለቲከኞች እንዳሉ የትላንቱና የዛሬው የሀገሪቱ ታሪክና ሁኔታ ማሳያዎች ናቸው።

**ወጣቶች የቤተ ክርስቲያናችንና የሀገረ ስብከታችን ጌጦች ናቸው። ወጣቶቻችን የእኛ አባቶች እጣፈንታዎች ናቸው። በወጣቶቻችን ደግሞ መሥራት ያለብንን ሁሉ እንሠራለን። ቤተ ክርስቲያን እንጠብቅበታለን፤ ሕዝቡን እናንጽበታለን፤ ማንኛውንም ተልእኮ እናከናውንበታለን። ወጣቱን ትውልድ በሃይማኖትና በምግባር አቅንቶ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት መጠቀም ዘመኑ የሚጠይቀው ተግባር ነው።**

ከዛሬ ፖለቲከኞች የወገንን ቁስል የሚጠግን ንግግር ሳይሆን የሚወጣው የሐሰት ትርክትና ድል አድራጊነት እንዲሁም ሕዝብን ከሕዝብ የሚያጋጭ ሀሳብ ነው። የራሳቸውን ጥሩ ኑሮ የሚኖሩ የሌላውን ኑሮ ደግሞ የሚያጨልሙ በርካቶች ናቸው። ትንኮሳውንና ብጥብጡን ሲፈልጉ የሃይማኖት እያደረጉ ካልሆነ ደግሞ የብሔር መልክ እያላበሱ ይኖራሉ። እነዚህን እግዚአብሔር ወደ ኅሊናቸው እንዲመልሳቸውና ወገናዊ ፍቅር እንዲኖራቸው እንጸልያለን።

በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል ዞን ያለውን የፀጥታ ችግር ለማስተካከል የክልል የፀጥታ ኃይልን ጨምሮ መከላከያና የፌዴራል ፖሊስ አባላት በቦታው ቢሰማሩም አሁንም ድረስ በአካባቢው በየቀኑ ሞትና መርዶ አለ። ሰዎች በግፍ ተፈናቅለዋል፤ በአካባቢያቸው ለዘመናት ያፈሩት ሀብት ንብረት ወድሞባቸዋል። ይህ ተግባር እንዲቆም ቤተ ክርስቲያን በተለያዩ ጊዜያት "ከታሪክ እንማር፣ ከክፉ ነገር እንመለስ እንዲሁም ለሀገር ሰላምና አንድነት እንቁም " እያለች ያለምንም ልዩነት ጥሪ እያቀረበች ነው።

***ስምዐ ጽድቅ፦*** የምእመናንና የቤተ ክርስቲያንን ደኅንነት ለመጠበቅ በሀገረ ስብከትዎ ያለው የወጣቶች አደረጃጀት ምን ይመስላል?

***ብፁዕ አቡነ አብርሃም፦*** ወጣቶች የቤተ ክርስቲያናችንና የሀገረ ስብከታችን ጌጦች ናቸው። ወጣቶቻችን የእኛ አባቶች እጣፈንታዎች ናቸው። በወጣቶቻችን ደግሞ መሥራት ያለብንን ሁሉ እንሠራለን። ቤተ ክርስቲያን እንጠብቅበታለን፤ ሕዝቡን እናንጽበታለን፤ ማንኛውንም ተልእኮ እናከናውንበታለን። ወጣቱን ትውልድ በሃይማኖትና በምግባር አቅንቶ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት መጠቀም ዘመኑ የሚጠይቀው ተግባር ነው። ቤተ ክርስቲያን ከወጣቶች የራቀና የተለየ አገልግሎት የላትም። ቤተ ክርስቲያን ወጣቶቿን በአብነት ትምህርት ቤትና በሰንበት ትምህርት ቤት አቅፋ ስታስተምር ቆይታለች። አሁን የምናያቸው ዲያቆናት፣ ካህናትና ጳጳሳት ከአብነት ትምህርት ቤቶች የወጡ ናቸው። እግዚአብሔርን የሚያመሰግኑና በሥነ ምግባር የታነጹ ወጣቶች ደግሞ ከሰንበት ት/ቤት የወጡ ናቸው።

ከጥንት ጀምሮ ቤተ ክርስቲያን ከወጣቶች የተለየ አገልግሎት ኖሯት አያውቅም። በሀገራችን በየአካባቢው ምእመናን ተገደሉ፣ ተፈናቀሉ፣ አብያተ ክርስቲያናት ተዘረፉና ተቃጠሉ የሚሉ ዜናዎችን መስማት እየተለመደ የመጣ ተግባር በመሆኑ እነዚህ እኩይ ተግባራት ወደ ሀገረ ስብከታችን ከመምጣታቸው በፊት ቅድመ ዝግጅት አድርገናል። ዘመኑ መለወጡንና አሰላለፉ መቀየሩን በመረዳታችን ወጣቶችን ማደራጀትና ማሰባሰብ ጀምረናል። ይህ ወጣት ሀገሩን ወገኑን እንዲወድና በሃይማኖቱ የቀና በሥነ ምግባር የታነፀ እንዲሆን እየሠራን ነው። ከዚህ ባሻገር ወጣቱ ትወልድ የቤተ ክርስቲያንና የምእመናንን ድኅነትን ተደራጅቶ እንዲጠብቅ ሥራዎች ተሠርተዋል፤ ወደፊትም በትኩረት ይሠራሉ። ወጣቶችን ለማሰባሰብ ሲታሰብ መጀመሪያ የተወሰደው ርምጃ የጽዋ ማኅበራትን ወደ አንድ ማሰባበብ ነው። ስልታዊ እቅድ ነድፈን ከቀን ሠራተኛ እስከ መንግሥት ሠራተኛ ድረስ ሕግና መመሪያን እንዲሁም የቤተ ክርስቲያኗን ሥርዓት የተከተለ አደረጃጀት ፈጥረናል። ለወደፊቱ ከተደራጁ ወጣቶች መካከል ቋሚ የሥራ እድል ያልተፈጠረላቸውን ወጣቶችን በመለየት የሥራ እድል የሚያገኙበትን መንገድ ማመቻቸት ቢቻልም መልካም ነው።

በባሕር ዳር ሀገረ ስብከት ሥር የተደራጁ ወጣቶች ‹‹የባሕር ዳር የወጣቶች ኅብረት›› የሚባል ሲሆን በማንኛውም የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ላይ ንቁ ተሳትፎ ያደርጋሉ፡ እነዚህ ወጣቶች በቤተ ክርስቲያንና በምእመናን ላይ ሲደርሱ የነበሩ ችግሮችን የቀረፉና ወንጀል ሲፈጽሙ የነበሩ አካላትንም ወደ ሕግ ሲያቀርቡ የቆዩ ናቸው። ወጣቶች አንድነታቸውን ባጠናከሩ ቁጥር ኃይል እንዳላቸውና ቤተ ክርስቲያናቸውን ከክፉ ነገር መጠበቅ እንደቻሉ አሳይተዋል። ለወደፊቱም የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ሁሉ ወጣቱን ያቀፈ ከሆነ ቤተ ክርስቲያን የማትሻገረው ፈተና አይኖርም ብዬ አምናለሁ።

***ስምዐ ጽድቅ፡-*** ቀረ የሚሉት ነገር ካለ?

ብፁዕ አቡነ አብርሃም፡- በእኛ ሀገረ ስብከት ያሉ የመንግሥት ባለ ሥልጣናት የቤተ ክርስቲያንን ትልቅነትና ኃያልነት የተረዱ በመሆናቸው ቤተ ክርስቲያን በምታዛቸው ጊዜ ሁሉ ታዛዥ ናቸው። ሃይማኖታቸው ምንም ይሁን ነገር ግን ሁሉም ለቤተ ክርስቲያን ቀና የሆነ አመለካከትና የታዛዥነት መንፈስ አላቸው። ቤተ ክርስቲያን ለሀገር ባውለታ መሆኗን በደንብ የተገነዘቡ በመሆናቸው እኛ ወደ እነርሱ ሳንሄድ እነርሱ ወደ እኛ መጥተው አስፈላጊውን ማኅበራዊ አገልግሎት ይሰጡናል።

በዚህም ቤተ ክርስቲያን ለመንግሥት አካላቱ እውቅና ትሰጣለች። ከባሕር ዳር የመንግሥት ባለ ሥልጣናት በሌሎች የሀገራችን ክፍሎች ያሉት ልምድ ሊወስዱና ሊማሩ ይገባል። ቤተ ክርስቲያንን በወራሪና በጠላትነት ፈርጀው በርሷ ላይ ጥቃት የሚፈጽሙና የሚያስፈጽሙ በተለይ የታችኛው የመንግሥት አካላት ከድርጊታቸው ተቆጥበው የመልካም ሥራዎች ተምሳሌት የሆኑ አካባቢዎች ላይ ልምድ ቢወስዱ መልካም ነው።

**ሰላምን ከሌላ አካል ከመጠበቅ ደግሞ እኛ የቤተ ክርስቲያን ልጆች ተናበንና ተግባብተን መሥራት መቻል አለብን። መናበባችን ከመንበረ ፓትርያርክ እስከ አጥቢያና ምእመናን ድረስ የሚደርስ መሆን አለበት። ቤተ ክርስቲያን ከሠራችው ያልሠራችው ይበልጣልና የቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያ ሥራ መሆን ያለበት የልጆቿን ሰላምና ደኅንነት ማስጠበቅ ነው።**

# ዐቢይ ጾም (ጾመ ሁዳዴ)

በእህተ ሚካኤል

የተወደዳችሁ የእግዚአብሔር ልጆች! እንደምን ከረማችሁ? ደህና ናችሁ? አሜን እግዚአብሔር ይመስገን!

ልጆች የአንደኛ ሰሚስተር ውጤት እንዴት ነው? መቼም ባለፈው ባስተላለፍንላችሁ ምክር መሠረት በደንብ አጥንታችሁ ጥሩ ውጤት እንዳመጣችሁ ተስፋ እናደርጋለን። በርቱ እሺ! ነገ አድጋችሁ የቤተ ክርስቲያንና የሀገር ተረካቢ የምትሆኑት እናንተ ናችሁ፤ ለዚህ ደግሞ በመንፈሳዊውም በዓለማዊውም እውቀት ማደግ አለባችሁ።

ልጆች! ዛሬ ይዘንላችሁ የቀረብነው ስለ ዐቢይ ጾም ወይም ስለ ጾመ ሁዳዴ ነው፤መልካም ንባብ ይሁንላችሁ!

ልጆች! በቅድስት ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ መሠረት በዓመት ውስጥ ሰባት የአዋጅ አጽዋማት አሉ። እነዚህን አጽዋማት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ተከታይ የሆነ ምእመን ሁሉ ከልጅ እስከ አዋቂ የሚጾማቸው ነው። ልጆች! በቤተ ክርስቲያን ሕፃናት ከሰባት ዓመታቸው ጀምሮ መጾም እንዳለባቸው ፤እንዲሁም አጽዋማት የአዋጅ እና የፈቃድ ተብለው እንደሚከፈሉ ከዚህ በፊት በጻፍነው ጽሑፍ ውስጥ ገልጠንላችሁ ነበር አስታወሳችሁ? ደህና።

ልጆች ዐቢይ ጾም(ጾመ ሁዳዴ) ከሰባቱ የአዋጅ አጽዋማት ውስጥ አንዱ ነው። ይህ ጾም ዐቢይ ጾም የተባለበት ምክንያት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የጾመው ጾም ስለሆነ ነው። ሌላው ደግሞ ከሌሎቹ አጽዋማት ብዙ ቀናት የሚጾም ጾም በመሆኑ ነው። ጾመ ሁዳዴ መባሉም ‹‹ሁዳድ›› ማለት ሰፊ የእርሻ ቦታ ወይም ማንኛውም ብዙ ሕዝብ የሚሳተፍበት ሥራ ማለት ነው። ይህም ጾም ታላቅ ጾም በመሆኑ እና ብዙዎች የሚጾሙት ጾም በመሆኑ ምክንያት ጾመ ሁዳዴም ይባላል።

ዐቢይ ጾም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ እጅ በዮርዳኖስ ወንዝ ከተጠመቀ በኋላ ሳይውል ሳያድር ዕለቱኑ ወደ ገዳመ ቆሮንቶስ በመሄድ ፵ ቀንና ፵ ሌሊት የጾመው ጾም ነው። ልጆች! ጌታችን የጾመው ኃጢአት ኖሮበት ሳይሆን ለኛ አብነት ለመሆን ነው። በዚህም መሠረት ዐቢይ ጾምን ከጌታችን ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ በኋላ ሐዋርያት ጾመውታል፤ እኛም ክርስቲያኖች እነሱን አብነት በማድረግ እንጾማለን።

ልጆች! የዐቢይ ጾም ወይም ጾመ ሁዳዴ ስምንት ሳምንታት እና ሃምሳ አምስት ቀናትን የያዘ ነው። እነዚህ ቀናት ሰባት ቅዳሜና ስምንት እሑድን ሲይዙ በአጠቃላይ አሥራ አምስት ቀን ይሆናሉ ማለት ነው። የዐቢይ ጾም ሃምሳ አምስት ቀናት ናቸው ስንል ጌታ የጾመው ፵ ቀናት ነው። ለምን ሃምሳ አምስት ቀን ሆነ? ሲባል ከጾሙ መጀመሪያ እና መጨረሻ ላይ የተጨመሩ ሁለት ሳምንታት ወይም አሥራ አምስት ቀናት ስላሉ ነው። እነሱም የመጀመሪያው ሳምንት ጾመ ሕርቃል ሲባል ፤ የመጨረሻው ሳምንት ሰሙነ ሕማማት በመባል የሚታወቅ ነው። እነዚህ ሁለት ሳምንታት የተጨመሩበት የራሳቸው ታሪክ እና ምክንያት አላቸው።

ልጆች የዐቢይ ጾም ሳምንታት የየራሳቸው መጠሪያም አላቸው። እነዚህንም የዐቢይ ጾም ሳምንታት የሰየመው የቤተ ክርስቲያናችን የዜማ ሊቅ የሆነው ቅዱስ ያሬድ ጾመ ድጓ በሚለው መጽሐፉ ነው። ስምንቱ የዐቢይ ጾም ሳምንታት መጠሪያዎችም:-

1. ዘወረደ
2. ቅድስት

3. ምኩራብ
4. መጻጉዕ
5. ደብረ ዘይት
6. ገብርኄር
7. ኒቆዲሞስ
8. ሆሣዕና በመባል ይታወቃሉ፡፡

በዚህ ክፍል ከስምንቱ ሳምንታት ስያሜዎች ሁለቱን ማለትም ‹‹ዘወረደ››ን እና ‹‹ቅድስት››ን አንስተን ለምን ይህ ስያሜ እንደተሰጣቸው በዝርዝር እናያለን፡፡

**1. ዘወረደ ፡-** ከዐቢይ ጾም ሳምንታት መካከል የመጀመሪያው ሳምንት ‹‹ ዘወረደ›› በመባል ይጠራል፡፡ ዘወረደ ማለት ከላይ የመጣ፣ የወረደ ማለት ነው፡፡ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አዳምንና ልጆቹን ለማዳን ሰው ሆኖ ወደዚህ ዓለም መምጣቱን፤ ለሰው ልጆች ሲል መከራ ሞት መቀበሉን፣ እንዲሁም በመስቀል ተሰቅሎ ዓለሙን ማዳኑን ያመለክታል፡፡ ‹‹ከሰማይ ከወረደው ከሰው ልጅ በቀር ወደ ሰማይ የወጣ የለም እርሱም በሰማይ የሚኖረው ነው›› ዮሐ ፫፥፲፫ ካለው ከጌታችን ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ቃል በመነሳት ይህ ስያሜ ተሰጥቶታል፡፡ ይህ ሳምንት ‹‹ጾመ ሕርቃል›› በመባልም ይታወቃል፡፡

ልጆች ሕርቃል የሚባል የቤዛንታይን ንጉሥ ነበር፡፡ እርሱ ንጉሥ በነበረበት ዘመን ፋርሶች ኢየሩሳሌምን በመውረር የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን መስቀል ማርከው ወደ ሀገራቸው ወስደውት ነበር፡፡ ንጉሡ ሕርቃልም ወደ ፋርስ በመዝመት የጌታን መስቀል ለማስመለስ ተነሣ፤ ነገር ግን ሐዋርያት በሲኖዶሳቸው ‹‹ነፍስ የገደለ ሰው እስከ ዕድሜ ልኩ ይጹም›› ብለው ሥርዓት ሠርተው ነበርና ፈራ፡፡ ይህን ፍርሃቱን የተረዱት የኢየሩሳሌም ምእመናንም ‹‹ጠላታችንን አጥፍተህ መስቀሉን አስመልስልን እንጂ ጾሙን አምስት አምስት ቀን ተከፋፍለን እኛ እንጾምልሃለን›› በማለታቸው ፋርስ ድረስ ዘምቶ መስቀሉን አስመልሷል፡፡ ቤተ ክርስቲያንም ይህንን ሥርዓት መሠረት በማድረግ እንዲሁም ሐዋርያትን አብነት በማድረግ የዐቢይ ጾም የመጀመሪያውን ሳምንት ‹‹ጾመ ሕርቃል›› በሚል ሰይማ እንዲጾም አድርጋዋለች፡፡ (ስንክሳር መጋቢት ፲፪)

**2. ቅድስት፡-** የዐቢይ ጾም ሁለተኛው ሳምንት ‹‹ቅድስት›› በመባል የሚታወቅ ሲሆን፤ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እኛ ክርኩስነታችን የምንቀደስበትን ሥርዓት ሊሠራልን በገዳመ ቆሮንቶስ መጾም መጀመሩን ቤተ ክርስቲያን ታስተምረናለች፡፡ ልጆች ቅድስት ማለት ጽኑዕ፣ ክቡር ማለት ነው፡፡ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለኛ አብነት ይሆነን ዘንድ ጾሙን የጀመረበት ሳምንት በመሆኑ ቅድስት ተብሎ ይጠራል፡፡

ይህ ሳምንት የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ ቅድስና የሚነገርበት ሳምንት ነው፡፡ ሰንበት የእረፍት ቀን እንድትሆን በኦሪትም በሐዲስም እግዚአብሔር አምላክ የቀደሳት ዕለት መሆንዋን የሚናገር፤ እግዚአብሔር ቅዱስ እንደሆነ የፈጠረው ሰውም ቅድስናን መያዝ እንደሚገባው የሚያሳስብም ነው፡፡ ዘፍ ፪፥፫፤ ፩ኛ ጴጥ ፩፥፲፭–፲፮፡፡ ባጠቃላይ ቅድስት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጾሞ የጾምን ጥቅምና ሥርዓት ሊያሥተምረን መጾም የጀመረበት ሳምንት ነው፡፡

ልጆች! ስለተቀሩት የዐቢይ ጾም ሳምንታት ስያሜና ትርጉም በሚቀጥለው እትማችን እናስተምራኋለን፤በሚቀጥለው ትምህርት እስከምንገናኝ ጾሙን እንድትጾሙና እንደትጸልዩ እንመክራችኋለን፡፡

*ደኅና ሰንብቱ ጾሙን የበረከት ያድርግላችሁ!*

# አክባሪ ያጣው ሕግ

**ኪኑኪሩ ከአዲስ አበባ**

በረከታቸው ይደርብንና ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለሃይማኖት ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን በጸሎት በትጋት ይመሩ በነበረበት ዘመን በ፲፱፻፸፱ ዓ.ም አንድ የወጣ ሕግ ነበር:: በጊዜው በአዲስ አበባና በዋና ዋና ከተሞች መነኮሳት ከገዳም ወጥተው በከተሞች የመመላለስ በዚያም የመቆየት ልማድ እየተንሰራፋ በመምጣቱ ከዚህ በፊት የነበረውን የሲኖዶስ ውሳኔ እና የአባቶች ምክር መነሻ በማድረግ አንድ ሕግ እንዲወጣ ተደርጎ ነበር::

መነኮሳት የፈቃድ ወረቀት ሳይዙ በከተማ ወይም ከገዳም ውጪ በሆነ ስፍራ እንዳይገኙ ተክከሏል:: ከገዳም ከወጡ የፈቃድ ወረቀት መያዝ አለባቸው:: ያለፈቃድ የሚገኙ በሕግ አካላትም እንዲጠየቁ መመሪያ ተላልፏል:: ቀሳውስትም ከአንዱ ሀገረ ስብከት ወደ ሌላው ሄደው ሀገረ ስብከት ዝውውር ለማድረግ ቢፈልጉ ከነበሩበት ሊቀ ጳጳስ የፈቃድ ወረቀት ማጻፍ አለባቸው:: ይህ ውሳኔ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስያን በ፲፱፻፵፯ ዓ.ም እና በ፲፱፻፶ ዓ.ም ባወጣችው በሁለተኛው ሲኖዶስ በ፲፩ኛው፣ በ፲፫ኛው፣ በ፲፬ኛው አንቀጽ እንዲሁም በሦስተኛው ሲኖዶስ በ፬ኛው ክፍል የተወሰነውን ውሳኔ መሠረት ያደረገ ነበር ተብሏል::

ይሁን እንጂ ይሄ ሕግና መመሪያ ከወጣበት ጊዜ አንሥቶ ላለፉት ሦስት ዐሠርት ዓመታት በአግባቡ ሳይተገበር እንደውም ከጊዜ ጊዜ በባሰ ሁኔታ የመነኮሳት ፍልሰትና አግባብ ያልሆነ የከተሞች ቆይታ መስተዋሉን ቀጥሏል:: ይህ ሁኔታ መልኩን እየቀየረም በገዳማት በሱባኤና በትጋት በሚቆይባቸው የጾም ወራትም ተከብሮ አለመገኘቱ ደግሞ የበለጠ ያሳስባል::

መነኮሳት ወደ ከተማ እንዳይመጡ ፈጽሞ የተከለከለ ባይሆንም ለገዳሙ በመላላክ፣ ወይም የእነሱን ወደ ከተማ መምጣት የሚያስፈልግባቸው የጋራና የግል ጉዳዮች ሲኖሩ የፈቃድ ወረቀት ይዘው እንዲንቀሳቀሱ ይፈቀዳል:: ይሁን እንጂ ምክንያቱ በማይታወቅ፣ ጥንቃቄ በጎደለው፣ ድፍረትም በተሞላባት፣ አሰናካይ በሆነ ሁኔታ በአዲስ አበባና በሀገራችን አንቱ በተባሉ ከተሞች በቁጥር በዛ ያሉ መነኮሳትን ማየት እየተለመደ ነው:: እነዚህ መነኮሳት በከተሞች የሚያደርጓቸው መመላለሶች ብቻ ሳይሆን በሚፈጽሟቸው ተግባራትም ለምእመናን ሰላም በማይሰጡ፣ ለቤተ ክርስቲያን ሥርዓት በማይመጥኑ፣ ለገዳማዊ ሥርዓቱ ክብር በነፈጉ ተግባራት ውስጥም ይታያሉ:: መነኮሳት ከገዳማት ሲመጡ የሚያርፉባቸው ገዳማት ሊኖሯቸው ሲገባ በየመንደሩ፣ በየሆቴሎች የሚቆዩ መኖራቸው፣ በሆቴሎችና በአደባባዮች ሲመገቡ የሚወሰድባቸው ትዝብቶች፣ አብረዋቸው በሚውሉና በሚንቀሳቀሱ ሰዎች ምክንያት የሚያሳድሩት አሉታዊ ተጽእኖ . . . ወዘተ በቤተ ክርስቲያኒቱ እየፈጠረ ያለው ማሰናካያ ግምቱ እየከበደ ነው::

በከተሞች ያለፈቃድ የሚንቀሳቀሱ አንዳንድ መነኮሳት ቆቡን አስተካክለው፣ መስቀላቸውን ይዘው፣ ቀሚሳቸውን አሳምረው፣ ፈረጅያቸውን ነስንሰው፣ ምንኩስናቸውን የበለጠ በሚገልጽ አለባባስ ስለሚታዩ መነኮሳት መሆናቸውን ማንም በግልጽ የሚረዳው ሆኖ ይታያሉ:: ነገር ግን አዲስ አበባን በመሰሉ ከተሞች በአውቶብሶች ላይ ባለው ግፊያ ውስጥ የሚደርስባቸው መንገላታት፣ ክብር ማጣት፣ ከዚያም አልፎ ለቁጣና ለክርክር የሚዳርግ ሁኔታ ለምእመናን ትልቅ ቁጭት የሚፈጥር ነው:: በታክሲዎች ውስጥ በተሳፋሪ ክብር ማጣት፣ በረዳቶች ማመናጨቅና ከንቱ ክርክሮች ውስጥ መታየት ለሥርኣተ ምንኩስናው የሚሰጠውን ክብር ያቀለዋል::

ከዚያ አልፈው በየመጠጥ ቤቶች አካባቢ፣ በየሥጋ ቤቶች ደጃፍ ተቀምጠው አገልግሎት ለማግኘት ሲውተረተሩ መታየቱም ለቤተ ክርስቲያን ቤተሰብ ሰላም የሚሰጥ አይሆንም:: በስመ መነኵሴ የሚነግዱ ፤መነኵሴ ሳይሆኑ

በተከበረው ልብስ ውስጥ ተደብቀው ‹‹ ወደ ገዳም ልሄድ ነውና ብር አምጡ›› እያሉ የዋሁን ምእመን ኪስ የሚያራቁቱ ብዙዎችን በየመንገዱ ማየት የተለመደ ከመሆኑም ባሻገር የቤተ ክርስቲያንንም ሆነ የእውነተኞቹን መነኮሳት ክብር የሚነካ ነው።

በስንት ተጋድሎ የሚገኘውን የክብር ልብስ በቀላሉ ከመርካቶ በመግዛት ተጎናጽፈው በቤት የክብር ወንበር፤ በአደባባይ የክብር ስፍራ ለማግኘት የሚሯሯጡ ‹‹የቀበሮ ባህታውያን›› በከተማው እንደ አሸን ፈልተው ሲታይ ደህነኛውን ለመለየት እጅግ አስቸጋሪ የሆነበት ዘመን ነው። ዛሬ ዛሬ ምንኩስና የእነ አባ እንጦንስን ፈለግ በመከተል ይህን ዓለም ንቆ ለእግዚአብሔር ማደሪያ መሆኑ ቀርቶ ወደ አውሮፓና አሜሪካ ለመሄድ ፓስፖርት ማግኛ መንገድም እየሆነ ነው።

ያለፈቃድ እንቅስቃሴ የሚያደርጉ መነኮሳት ሌላም ቀዳዳ እየከፈቱ ነው። መነኩሴ ሳይሆኑ መነኩሴ መስለው ለሚንቀሳቀሱ መናፍቃን በአርአያ ምንኩስናው የቤተ ክርስቲያንን ገጽታ በማበላሸትና የተሳሳተ ትምህርት በመስጠት ያሉትን የቤተ ክርስቲያን ቤተሰቦች ከቤተ ክርስቲያን እንዲወጡ ያልገቡትን ደግሞ በዚያው ሳይገቡ እንዲቀሩ በማድረግ ወጥመድ ለዘረጉ ክፉዎች በር ከፍተዋል።

የቤተ ክህነቱ አስተዳዳርም ከዚህ በፊት እንደዚህ ያሉ እንቅስቃሴዎችን ለማስተካከል ያወጣው ሕግ እንዳለ እያወቀ ከሚመለከታቸው የሕግ አካላት ጋር በመተባባርም ድርጊቱን ማስቆም አልቻለም። መነኮሳት ከገዳም የሚወጡበትንም ሁኔታ በትክክል ለማስተግበር የሚስችል ግልጽ አሠራር ከገዳማት ጋር በመተባባር አላዳበረም። ስለዚህ ተግባሩ የሁልጊዜም የቤተ ክርስቲያን ሐዘን ሆኖ ቀጥሏል።

አጅግ አስገራሚው ነገር ደግሞ ምእመናን ካሉባቸው ብዙ ጭንቀቶች የተነሣ ዕረፍት ይሰጡናል ወደሚሏቸው ገዳማት በስፋት እየተመሙ፣ በጾም በሱባኤ ለመቆየት ከፍተኛ ፍላጎት እያሳዩ ባሉበት በዚህ ዘመን የመነኮሳት ከገዳም ወጥቶ በከተሞች መሰንበት ነገሩን እንዴት በተቃራኒ እየተጓዘ እንደሆነ የሚያመላክት ነው።

በመሆኑም የቤተ ክርስቲያን አስተዳዳር ከዚህ በፊት ያወጣቻቸውን ሕጎች/መመሪያዎች አሁንም ለማንቃት ቢሞክር መልካም ይሆናል። ገዳማትም እየተጎዳ ያለው ሥርዐተ ምንኩስናው የገዳማዊ ሕይወት ክብር መሆኑንን በውል ተረድተው የውስጥ አስተዳዳር ሥርዐቱን ማርቀቅ ይገባቸዋል። ያሏቸውን ሴትና ወንድ መነኮሳት ቁጥር ማወቅ ማንነታቸውን መለየት ሕጋዊ መታወቂያ መስጠት፣ በገዳሙ ሥርዐት መሠረት የመነኮሳትን እንቅስቃሴ ምን መምሰል እንዳለበት ሥርዐታቸውን በየጊዜው ማጥበቅ ይገባቸዋል።

ምእመናንንም አጓጉል እንቅስቃሴ የሚያደርጉ መነኮሳት መደበቂያ ዋሻ ከለላና ጠበቃ በመሆን የቤተ ክርስቲያንን ሥርዐታዊ አሠራር ከማወክ ሊቆጠቡ ይገባል። ሰንበት ትምህርት ቤቶችና ማኅበራት በዚህ ረገድ ያለውን ጥፋት ከግምት ያስገባ እርምጃ መውሰድም ያስፈልጋቸዋል።

**ያለፈቃድ እንቅስቃሴ የሚያደርጉ መነኮሳት ሌላም ቀዳዳ እየከፈቱ ነው። መነኩሴ ሳይሆኑ መነኩሴ መስለው ለሚንቀሳቀሱ መናፍቃን በአርአያ ምንኩስናው የቤተ ክርስቲያንን ገጽታ በማበላሸትና የተሳሳተ ትምህርት በመስጠት ያሉትን የቤተ ክርስቲያን ቤተሰቦች ከቤተ ክርስቲያን እንዲወጡ ያልገቡትን ደግሞ በዚያው ሳይገቡ እንዲቀሩ በማድረግ ወጥመድ ለዘረጉ ክፉዎች በር ከፍተዋል።**

ይህ ካልሆነ ገዳማዊ ሥርዐት የማይወደድ የማይፈለግ፣ ከዓለማዊ አኗኗር ያልተለየ እንዲመስል ያደርገዋል። የዋህና ትሑት አባቶች በፈቃድ ሲንቀሳቀሱ የሚገባቸውን ክብርና ነጻነት እንዳያገኙ ወጥመድ ይፈጥራል። ለመናፍቃን እንቅስቃሴ አመቺ መንገድ ይከፈታል። የቤተ ክህነት አስተዳደር አቅምም ጥያቄ ውስጥ ይገባል። ስለዚህ ሳይቃጠል በቅጠል የሚለውን ብሂል ማሰብ ይገባል።

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*

# ንሰሐ አባቴን የደበቅሁት ምሥጢር፦ ወደ ኋላ መመለስ ፈራሁ

**ክፍል ሁለት**

***የተወደዳችሁ አንባብያን የዚህን ጽሑፍ የመጀመሪያ ክፍል ከዚህ በፊት በነበረው እትም ላይ ማቅረባችን ይታወሳል። ቀጣዩንና የመጨረሻውን ክፍል ደግሞ እንደሚከተለው አቅርበነዋል።***

## ፫. ቅዱስ ጴጥሮስ

በሐዲስ ኪዳን ደግሞ በኃጢአቱ ምክንያት ከእግዚአብሔር ጋር ተጣልቶ ግን ንስሓ በመግባቱ ከታረቁት መካከል በዋናነት ሊቀ ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስ ተጠቃሽ ነው። ይህ ሐዋርያ ሌሎች እንኳ ቢክዱህ እኔ አልክድህም ሲል የነበረ ቢሆንም ከሌሎቹ ተለይቶ የካደ እርሱ ነበር። ሆኖም ግን በፍጥነት ወደራሱ ተመለሰ። የተነገረው ትንቢት ሳይውል ሳያድር እንደተፈጸመበት አወቀ። ፈጥኖ አለቀሰ፤ ንስሓ ገባ፤ እግዚአብሔርም ይቅር አለው። የጥሉ ግድግዳ በንስሓው አማካኝነት በእግዚአብሔር ቸርነት ተናደ። በዚህም ታማኝ አድርጎ የበጎቹ ጠባቂ አደረገው። (ዮሐ.፳፩፥፲፭-፲፰) ስለዚህ ምንም እንኳ ኃጢአተኛው የሠራው ክፉ ሥራና የሚገባው ንስሓ ማለትም በንስሓ የሚያደርገው ጸሎት፣ ልመና፣ ልቅሶ፣ ስግደት፣ ምጽዋት ወዘተ ለበደለው በደል በትክክል ካሳ ከመሆን አንጻር ባይመጣጠንም እግዚአብሔር ግን በባሕርዩ መሐሪ ነውና ንስሓውን ምክንያት አድርጎ ይቅር አለው ታረቀውም።

## ፬. ማርያም እንተ ዕፍረት

ማርያም እንተ ዕፍረት ዕድሜ ዘመኗን በኃጢአት ያሳለፈች ሴት ነበረች። ይሁን እንጂ በኃጢአት መኖር ከእግዚአብሔር መለየት አግባብ እንዳልሆነ በተረዳች ጊዜ ፈጥና ወደ ንስሓ ተመለሰች። በቅዱስ ወንጌል ተጽፎ እንደምናገኘውም እጅግ ዋጋው የከበረ ሽቶ አቀረበች ጌታችን መድኃኒታችንንም በእንባዋ አጠበችው። የንስሓ ዋጋ የሆነውንም "እውነት እላችኋለሁ ይህ ወንጌል በዓለሙ ሁሉ በሚሰበክበት ቦታ ይህች ሴት ያደረገችው ለእርሷ መታሰቢያ ሆኖ ይነገራል።" በማለት የማይጠፋ ስም ሰጣት። (ማቴ.፳፮፥፮-፲፫)፤ (ማር.፲፬፥፫-፱)፤ (ዮሐ. ፲፪፥፩-፰)

ከማርያም ዕንተ እፍረት የምንማራቸው በርካታ ቁም ነገሮች አሉን እነሱም ለበጎ ነገር መሽቀዳደምን ይልቁንም ለንስሓ ጊዜ መስጠት እንደሌለብን እንረዳለን። ትርጓሜ ወንጌል እንደሚነግረን ማርያም እንተ ዕፍረት ይህ ቀረሽ የማትባል መልከ መልካም ነበረች። ከዕለታት አንድ ቀን መላ ሰውነቷን በሚያሳይ በቁም መስተዋት ራሷን እየተመለከተች ግን ያን የሚመስል ውበት እንደሚያልፍ እንደሚረግፍ ተገነዘበች። ለዚህ መድኃኒቱ ደግሞ ንስሓ መግባት እንደ ሆነ ተረዳችና ዘመኗን ሙሉ በዝሙት የአጠራቀመችውን ገንዘብ በመያዝ ሥርየትን ለሚያድለው፣ ኃጢአትህ/ሽ ተሥርዮልሃል/ሻል ለሚለው ሊቀ ካህናት መድኀነ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ የሚገባውን ሽቱ ገዝታ ወደ እርሱ ሄደችና ማድረግ የሚገባትን አደረገች።

ማርያም እንተ ዕፍረት ልቧ በተመለሰ ጊዜ ሳትውል ሳታድር ፈጥና ነው ንስሓን ወደ ሚቀበለው ሊቀ ካህናት የሄደችው። ይህ ብቻ አይደለም በመንገድ ላይም ሆነ ከደረሰች በኋላ በርካታ መሰናክሎች ገጥመዋታል። ከነዚህም መካከል ጥንት ዝሙት ያሠራት የነበረው ሰይጣን ቀድሞ በግብር ከሚያውቋት ወንድ ባንዱ ተመስሎ ከመንገድ ጠብቆ በርካታ የማሰናከያ ቃላትን እየጠቀሰ ሊያሰናክላት ሞክሯል። እሷ ግን አንድ ጊዜ ስለወሰነች እርሱ በሚያመጣው መሰናክል ሳትሸነፍ ለሚያነሣቸው ጥያቄዎች ሁሉ ተገቢውን ምላሽ እየሰጠች በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ድል ነሥተዋለች። ስለዚህ እኛም ወደ መልካም ነገር ስንሄድ በየመንገዱ እየጠበቀ ለዚያውም በምናውቀውና በምንወደው አካል

እያደረ እንዳያሰናክለን ትጥቃችንን ልናጠብቅ ይገባናል፡፡

ሌላው ከደቀ መዛሙርቱ የመጣው ፈተና ነበር፡፡ አዛኝ ለድሆች በጎ አሳቢ በመምሰል ይህ ተሸጦ ለድሆች በተሰጠ በተገባ ነበር በማለት ያደረገችውን ሥራ እንደጥፋት ቆጥረውት ነበር፡፡ ክርስቶስ ግን መልካም አደረገች ለምን ታሰናክሏታላችሁ በማለት ሥራዋን አደነቀላት፡፡ እንዲያውም ይህ የእሷ ሥራ በአራቱም ወንጌላውያን ሲነገር እንደሚኖር በመግለጽ አስረዳቸው፡፡ ዛሬም እኛ ለንስሓ መፋጠን እንጂ መዘግየት እንደሌለብን፣ እኛ ለንስሓ በተፋጠን ቁጥር እግዚአብሔር አምላካችን ንስሓችንን በቶሎ እንደሚቀበለንና የሚመጡ መሰናክሎችን ሁሉ የምናልፍበትን ኃይል እንደሚሰጠን ያስረዳናል፡፡

ምሕረትን ለሚያድለው፣ ኃጢአትህ/ሽ ተሠርዮልሃል/ሻል ለሚለው ሊቀ ካህናት መድኀነ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ የሚገባውን ሽቱ ገዝታ ወደ እሱ ሄደችና ማድረግ የሚገባትን አደረገች፡፡

ውድ እኅታችን ወለተ ገብርኤል ዛሬ ላይ ሁነሽ ይህን ጉዳይ መደበቅሽ የኅሊና ዕረፍት እንደነሣሽ የተደረገበት ምክንያት በዕድሜ የመብሰልሽ ጉዳይ ነው፡፡ ሰው በዕድሜ እየበሰለ በሄደ ቁጥር ትላንት ይጓዝበት የነበረው የጨለማ መንገድ አውቆም ይሁን ሳያውቅ ይሠራቸው የነበሩ ስሕተቶች በጉልህ እየታዩት ራሱን እንዲወቅስ፣ መሳሳቱንም እንዲያይ፣ እግዚአብሔር ኅሊናን ያህል ዳኛ መስጠቱ በዚህ ይታወቃል፡፡ የኅሊና ዳኝነት ከባድ ነው፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለሮሜ ምእመናን በላከው መልእክቱ "በልባቸው የተጻፈውን የሕግ ሥራ ያሳያሉ፤ ከሥራቸው የተነሣ ይታወቃል፤ ሕሊናቸው ይመሰክርባቸዋል፤ ይፈርድባቸዋልም" (ሮሜ ፪፣፲፭) በማለት እንደተናገረው ኅሊና በራሱ ስለሚጠይቅ ተፈጥሯዊ ጉዳይ መሆኑንም ልብ ማለት ያስፈልጋል፡፡

አንቺም የኅሊና ዳኝነቱ ደርሶሽ መፍትሔ ፍለጋ ጥያቄሽን አቅርበሽልናል፡፡  ወለተ ገብርኤል በቅድሚያ መረዳት የሚገባሽ ዝሙትን መፈጸም ከዐሥርቱ ትዕዛዛት አንዱን መሻር እንደሆነ መገንዘብ ይገባሻል፡፡ እግዚአብሔር አምላክ ለሊቀ ነቢያት ሙሴ ሕግን ሰጠው፡፡ በተሰጠው ሕግ ለወቅቱ እስራኤል ዘሥጋ (ያዕቆባውያን) ይተዳደሩበት ዘንድ ሲሆን ለፍጻሜው ደግሞ ለእስራኤል ዘነፍስ (ለክርስቲያኖች) የተሰጠ ሕግ ነው፡፡ ከዐሥርቱ ሕግጋት አንዱም ‹‹አታመንዝር›› የሚል ነው (ዘፀ. ፳፥፲፬፡፡) አንቺ ግን በወጣትነትሽ ወቅት በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ይህን ሕግ ተላልፈሽ ከተለያዩ ወንዶች ጋር ተራክቦ መፈጸምሽን ነግረሽናል፡፡

ወለተ ገብርኤል ዝሙት ታላቅ ኃጢአት መሆኑን በሰብአ ትካት በኖኅ ዘመን ሰዎች ላይ ያስከተለውን መዓት ምን እንደሆነ ታላቁ መጽሐፍ ይመሰክራል፡፡

በሐዲስ ኪዳንም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ክርስቲያኖች ከዝሙት ይርቁ ዘንድ ‹‹ሥጋ ግን ለእግዚአብሔር ነው እንጂ ለዝሙት አይደለም ጌታም ለሥጋ ነው፡፡ ሥጋችሁ የክርስቶስ ብልቶች እንደሆኑ አታውቁምን? እንግዲህ የክርስቶስን ብልቶች ወስጄ የጋለሞታ ብልቶች ላድርጋቸውን? አይገባም፡፡ ወይስ ከጋለሞታ ጋር የሚተባበር እንደሥጋ እንዲሆን አታውቁምን? ሁለቱ አንድ ሥጋ ይሆናሉ ተብሏልና፡፡ ከጌታ ጋር የሚተባበር ግን አንድ መንፈስ ነው፡፡ ከዝሙት ሽሹ፡፡ ሰው  የሚያደርገው ኃጢአት ሁሉ ከሥጋ ውጭ ነው ዝሙትን የሚሠራ ግን በገዛ ሥጋው ላይ ኃጢአትን ይሠራል፡፡ ወይስ ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደሆነ አታውቁምን? በዋጋ ተገዝታችኋል ለራሳችሁ አይደላችሁም ስለዚህ በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ፡፡›› በማለት አስተምሯቸዋል፡፡ ፩ቆሮ.፮፥፳–፳፫፡፡

ክርስቲያን በዋጋ የተገዛ መሆኑን ሲዘነጋ ለኃጢአት ይዳረጋል፡፡ ክርስቲያኖችን ጌታችን በወርቅ ደሙ እንደዋጀን ሐዋርያው ሲገልጽ "በዋጋ ተገዝታችኋል" አለ፡፡ ከዚህም በተጓዳኝ ዝሙትን ስንፈጽም በእኛ ያደረውን የእግዚአብሔርን መንፈስ ማሳዘን ስለሆነ ክርስቲያን በሕይወት ዘመኑ ሁሉ በሥጋው እግዚአብርን ማክበር ደግሞ ካልቻለና በማወቅም ሆነ ባለማወቅ በኃጢአት ከወደቀም ፈጥኖ ንስሓ መግባት ይጠበቅበታል፡፡

ወለተ ገብርኤል እንደሚታወቀው ኃጢአት የሥጋም የነፍስም በሽታ ነው፡፡ ለዚህ በሽታ ደግሞ እግዚአብሔር የሰጠን መድኃኒት ንስሓ ነው፡፡ የንስሓ ሁሉ መጀመሪያ ደግሞ የኅሊና ወቀሳ ነው፡፡ ይህም ማለት ኃጢአተኝነትን ማመንና ኃጢአትን ማውገዝና መጥላት ነው፡፡ ይህም ተነሳሒው በኅሊናው በአንቺ እንደሆነው ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር መናዘዝ ነው፡፡ ‹‹ኃጢአቴን ለአንተ አስታወቅሁ በደሌንም አልሸፈንሁም ለእግዚአብሔር መተላለፌን እናገራለሁ›› (መዝ. ፴፩፥፭ ) እንዲል፡፡

ይህ ዓይነቱ የኅሊና ጸፀት ብቻ በራሱ በቂ አለመሆኑን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በለምጽ በሽታ የተያዘውን ሰው ከለምጹ ከፈወሰው በኋላ ‹‹ሄደህ ራስህን ለካህን አሳይ›› (ማቴ.፰፥፬) ብሎታል፡፡ አንድ ኃጢአተኛ ራሱን ለካህን ማሳየት ለምን ያስፈልጋል? የሚል ሰው ካለም መልሱ የእግዚአብሔር ትዕዛዝ ስለሆነ ነው፡፡ ‹‹ካህኑ ሁሉን የሚችል የእግዚአብሔር መልእክተኛ ነውና ከንፈሮቹ ዕውቀትን ይጠብቁ ዘንድ ይገባቸዋል፤ ሕጉንም በልቡ ይመረምር ዘንድ ሚል.፪፥፯ ተብሏልና ነው፡፡

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሐዲስ ኪዳን ለወቅቱ ለቅዱሳን ሐዋርያት ለፍጻሜው በእርሱ እግር ተተክተው ለሚያገለግሉ ሥልጣነ ክህነት ላላቸው ካህናት የሰጠው ሥልጣን እንዲህ የሚል ነው፡፡ ‹‹እውነት እላችኋለሁ በምድር የምታስሩት ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል በምድር የምትፈቱት ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል፡፡›› (ማቴ.፲፰፥፲፰)

ይህ ሥልጣን በዘመናት፣ ኃያላን የማይሽሩት አምላካዊ ጸጋ ነው፡፡ እኅታችን ወለተ ገብርኤል እስቲ አንቺ አንድ ጥያቄ መልሽልን እንጠይቅሽ፡፡ አያድርገው እንጂ አምላከ ቅዱሳን ልዑል እግዚአብሔር በሥጋሽ ታመሽ ትላንት የጤና ባለሙያ ጋር ሄደሽ ሕመምሽን ተናግረሽ መድኃኒት ታዝዞልሽ ነገር ግን የታዘዘልሽን መድኃኒት በአግባቡ ባለመውሰድሽ ሕመሙ ቢጸናብሽ ተመልሰሽ ጤና ባለሙያው ዘንድ መሄድሽ ይቀራል? አይቀርም፡፡ ምክንያቱም ፈውስ ስለምትፈልጊ ተመልሰሽ ሄደሽ ተናግረሽ የሚታዘዝልሽን መድኃኒት ወስደሽ እንደምትጠቀሚበት ሁሉ ያለ ምንም ዕፍረትና ይሉኝታ የነፍስ አባቴ ዳግመኛ ስነግራቸው ምን ይሉኛል ሳትይና ሳትሳቀቂ ጉዳዩን በዝርዝር አስረድተሻቸው ያንጊዜ ያልተናገርኩት ዕፍረት ይዞኝ ነው፡፡ አሁን ግን ኅሊናዬን ኃጢአቱ እረፍት ስለነሳኝ ነው ብለሽ ተናዘሽ የሚሰጥሽን ቀኖና በተግባር ፈጽሚው፡፡

ነቢየ ልዑል ኢሳይያስ ‹‹እንድትጸድቅ መጀመሪያ ኃጢአትህን ተናገር›› ኢሳ.፵፫፥፳፮ ብሏልና፡፡ ከተለያዩ ወንዶች ጋር በዝሙት ኃጢአት መውደቅሽን መግለጽ ያለብሽ ለነፍስ አባትሽ ብቻ እንጂ ለትዳር አጋርሽ ለልጆችሽ አባት አለመሆኑንም ማወቅ ይገባሻል፡፡ ምክንያቱም አንደኛ የቀደመ በደልሽን የሚያስተሠርይልሽ ኃጢአትሽን ለካህኑ መንገርሽ እንጂ ለባለቤትሽ መንገረሽ አይደለም ባለቤትሽ ወደ ኋላ ተመልሰሽ የተደረገውን ድርጊት ስትነግሪው ኀልማሳ በሚስቱ ቀናዒ ነው ስለሚባል ሊከፋውና ሊጠላሽ ይችል ይሆናልና፡፡ ስለዚህም አሁን ማድረግ የሚገባሽ ከላይ እንደገለጽንልሽ የተደረገውን ድርጊት ኅሊናሽን ዕረፍት የነሳሽን ጉዳይ ለነፍስ አባትሽ ነግረሽ ንስሐ ግቢበት አይከብድም፡፡ በተጓዳኝ ደግሞ በመጽሐፍ ‹‹የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይልን ታደርጋለች›› (ያዕ.፭፥፲፮) ተብሏልና መብዓ ማለትም (ዕጣን፣ ጧፍ፣ ዘቢብ) ወደ ገዳማት ከስመ ክርስትናሽ ጋር በመላክ በጸሎት እንዲያስቡሽ አስደርጊ፡፡

በተቀረው በዘመንሽ ሁሉ በማወቅም ይሁን ባለማወቅ በፈጸምሽው ኃጢአት እየተጸጸትሽ መኖር አንዱ የክርስትና ሕይወት መሆኑን ብታውቂም እግዚአብሔር ደግሞ መሐሪ መሆኑን ሳትዘነጊው አምነሽ ኅሊናሽን በፀፀት ከመጉዳት ተጠበቂ፡፡ ቸሩ አምላክ በደልሽን ሁሉ ይቅር ብሎሽ ትዳርሽን ባርኮ እንዲቀድስሽ የእርሱ መልካም ፈቃድ ይሁን አሜን፡፡